# የእግዚአብሔር ድምጽ በነዚህ የመጨረሻ ቀናት

ዛሬ ማለዳ ዳግም በእነዚህ የስፔን ሰዎች መካከል መገኘት መታደል ነው። ጂም ይህንን እየቀዳ እንደሆነ እገምታለሁ። አዎ፤ ቅጂውን እየቀዳው ነው። ከወንድም ጋርሲያ ጋር ከዚህ በፊት እዚህ በነበርኩበት ጊዜ የስፔን መዘምራን ቡድን የሰሩት ቅጂ እስከ አሁን ድረስ ይዣለሁ። እና ሲዘመሩልኝ የነበረችው ትንሿ ዝማሬ እረሰቻታለሁ። ግን ፣ ኦህ ፣ ምን ያህል እንደምወዳት! እና ልጆቹ አሁን ሁሉም አድገው አግብተዋል። ያኔም አሁንም እንጠያየቃለን። በዚህ ማለዳ ደርሼ ህጻን ዮሴፍን በማየቴ፤ በውስጤ ልዩ ነገር ፈጥሮብኛል፤ በርግጥ እናንተን በማየቴም ደስ ብሎኛል።

2 እናም ፣ አሁን ፣ አንድ የስፓኒሽ ቃል መናገር ችያለሁ። መስማት ትፈልጋላችሁ? “ሃሌሉያ!” ያቺ መስማት የተሳናትን ሴት እንድትሰማኝ… ሰሞካክራቸው የነበሩትን ቃላት በፍጹም አልረሳቸውም። አሁን፤ ምናልባት ሁሉንም በተሳሳተ ልላቸው እችል ይሆናል፤ እያችሁ፤ ግን፤ በጣም የማስታውሰው “ኦየ።” ትክክል ነኝ? **ሰሙኝ**፤ **ሰሙኝ**፤ “ኦየ።” ደግሞም በፍጹም የማይረሳኝ፤ “ግሎሪያ አዲዮስ!” የሚደንቅ ነው! ኦ፤ በዋና ከተማዋ ሜክሲኮ ሲቲ ወርጄ፤ እነሱን ለማነጋገር፤ እድሉ አገኘሁና። እንዴት ደስ እንዳለኝ! እና እኔ…

3 ከዚህ ከተመልሰኩ በኋላ ወደ ፊንላንድ ሄድኩና። ሁልጊዜ ያቺ ያነጋገርኳት ትንሿ ፊንላንዳዊት ሴት ያስታውሰኛል። “ቤታኒ” ብለው ወደ ሚጠሩት ሰፍራ ወሰዱኝ። መቼም በየአገሩ የየራሱ አስተሳሰብ ይኖራል። (እስቲ፡ ያስተጋባል እንዴ? በጣም ተጠግቼዋለሁ፤ በደንብ ይሰማል? አሁን ጥሩ ነው።) ሴትየዋ ፣ መልከ መልካም ሰው ናት። እንደ እኔ ዓይነት፤ መጫወት የምትወድ ናት። አስተርጓሚው… በፍጥነት ስለምታወራ፤ እና—አስተርጓሚው ለመናገር የፈለገችውን ፈጥኖ መናገር አልቻለም። እና ቆም ብላ ፊቷ ቀይ ሆኖ፡- “በባቢሎን ላሉ ሰዎች የምለው ነገር አለኝ” አለች።

4 ታውቃላችሁ ግን፤ ወፎች ሁሉ— በእንግሊዝኛ እንደሚዘምሩ፤ ውሾች በእንግሊዝኛ እንደሚጮሁ፤ አስተውያለሁ፤ ሕፃናት በእንግሊዘኛ ያለቅሳሉ። እንደው እኛ ምን ሆነን ነው እላለሁ። ግን የኛ የየራሳችን—ቋንቋ የሺው ዓመት ቋንቋ እንዲሆን አርገን እናሰባለን፤ አዎና። ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስን ለተቀበልን ሰዎች ግን፤ ቋንቋችን ሰማያዊ ስለሚሆን፡ ይህ እውነት ነው።

5 የዋሽንግተን ዲፕሎማት ወንድማችን ሮው፤ ዛሬ ጠዋት ከእኛ ጋር አለ። ከአምስት ስድስት ፕረዚደንት፣ ከሰባት መሪዎች በታች እንዳገለገለ ይመስለኛል። ይሄን የመሰለ ሰው ከጀርባየ ተቀምጦ፤ በዚህ መድረክ፤ ቆሜ ስናገር፤ ምን እንደሚሰማኝ ታውቃላችሁ። በተለይ ግን ምስክርነቱ ሁልጊዜ፡ ለእኔ እጅግ ድንቅ ነው፡ ደግሞም በተጨማሪ… ሉተራን እንደነበረ አምናለሁ፤ ካልተሳሳትኩ፡ ካቶሊክ ወይ ሉተራን መሰለኝ፤ ሉተራን። እና እሱ…

የጴንጤቆስጤ የዳስ ጉባኤ ውስጥ ስለመንከባለሉ ይናገራል፤ ከዛ በኋላ ተነሳ... ወድያውም ወደ መሠዊያው ሄደ፤ እና፤ ሲሄድም፤ ጌታ በላዩ ላይ መጣና እጅግ ባረከው... በሰባት የተለያዩ ቋንቋዎች መናገር እኪችል ድረስ መሰለኝ። አንዱን ሞከርኩ፤ "አልሆነም፤" ከዛ ሌላውንን ሞከርኩ፤ "አልተሳካም" ይላል። እናንተ የምትችሉትን ያህል ስፓኒሽ ይናገራል። ስለዚህ—ሁሉንም ሞከራቸው፤ አልሰሩለትም። እናም፤ እዩት፤ የሆነውን ታውቃላችሁ፤ ጌታ መልካም ነው፤ ወርዶ ሞክሮት የማያውቀውን ቋንቋ ሰጠው፤ ከዛ "ተሳክቷል" አለ። ልክ ነው። እንደማሰበው በላይም የሚሆነው ይህ ይመስለኛል።

6 ስለ ትንሿ ቤተክርስቲያን በልቤ ውስጥ ብዙ ትዝታዎች ይዣለሁ፤ አምኛለሁና... ኦ፤ የት ነበረ እረሳሁ። አዎን አስታወስኩት። ወደ ቶንቶ ጎዳና አቅራቢያ እዚያ ጋር ነው። የሰፔን ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የነበረችበት ቦታ፤ "ቶንቶ ጎዳና፤" የሚል ቃል ትዝ ይለኛል።

7 ፓስተሩን "እዚህ ቦታ ሪቫይቫል ለማድረግ ይመቻል" ስለው ነበር። ብዙ ክፍሎች፤ አዲስ ቤተክርስቲያን፤ ጥሩ ህዝብ። ስለዚህ አንድ ቀን ሪቫይቫል ለማድረግ ታሳቢ ይሆናል ብዬ አሰባለሁ። ገብተን ሪቫይቫል እንድናደርግ፤ ጸልዩበት። አሁን፤ በሌላው ቤተክርስቲያን ያደረግነው መድገም ነው ተሰፋየ። በግቢው ውስጥ፤ አጥሩን ተደግፌ፤ ጎዳናውን ወደ ላይ እና ወደ ታች ስቃኝ፤ ሌሊቱን በዚያ ለማሳለፍ፤ ፈጽሞ የማልረሳ አስደሳች እንደነበር ትዝ ይለኛል። እና—እነዚያ ሴቶች፤ ወይዛዝርት እና ወንድሞች የዝማሬዎች ቅጂው አሁንም እኔ ጋር አለ። "ኦንሊ ቢሊቭ" ለመዘመር ሲሞክሩ፤ ታቃላችሁ፤ በትክክል ግን አልዘመሩትም። "ኦንሊ ቢሊቭ" ለማለት ፈልገው፤ "የኦና ቢሊቭ" ይላሉ።

8 ልጄ ሣራ እና ርብቃ፤ "አባዬ፤ ያቺ አጭር ቅጂ፤ የህጻናት መዝሙር፤ አጫውትልን... " ሲሉኝ ትዝ ይለኛል። "ስፓኒሽ" ለማለት ፈልገው፤ ቃሉን ማለት አይችሉትምና፤ እንዲህ ይላሉ፤ "የስፒናች ሴቶች፤ የስፒናች ህጻናት ሴቶች የሚዘምሩትን 'ኦንሊ ቢሊቭ።'"

9 አዎ፤ ጉባኤውን መሳተፋቸውን አስታውሳለሁ። ሪቫይቫሉ ለእነሱ ነበር፤ ጉባኤውን እስከ ዌስት ኮስት ድረስ ተሳትፈውበታል። እና... ካሊፎርኒያን ትተናት ስንወጣ አንዲት ነገር በልቤ ቀረች፤ ወንድም ሙር እና እኔ፤ እና ወንድም ብራውን ካፒቶል ላይ ነበርን። እና በዚያ ማታ ከህንጻው እየወረድኩ፤ ልጆቹ እዚያ ቆመው፤ "እርሱ ስለ አንተ ያስባል።" እየዘመሩ ነበር። ሰምታችሁታል እናንተም። "በፀሐይ በጥላዎችም ሁሉ፤ እሱ ስለ አንተ ያስባል።" ብዙውን ጊዜ ሌላ አገር ላይ፤ በዓለም የሰልፍ ጦርሜዳዎች፤ የክርስቶስን መልእክት ለማምጣት ስታገል፣ እነዚያ ሴቶች እና ወንዶች ልጆች የዘመሩትን ዜማ አስታውሳለሁ፤ "ስለ አንተ ያስባል። በፀሐይ ጨረር እና ጥላዎች አሁንም ስለ አንተ ያስባል።" ስለዚህ እጅግ የሚያበረታ፤ የሚያግዝ ነው።

10 ፓስተራችሁን ማግኘቴ፤ ቤተክርስትያኒቱም ህያው ሆና ማየቴ ደስ ብሎኛል ይህ ሁሉ የተቀናጀለት፤ የመኪና ማቆሚያ ክፍሎች የያዘ፤ ታላቅ ቆንጆ ህንፃ አግኝታቿል። በመንፈስ ቅዱስ እጅ ውስጥ ያለ ውብ ሰፍራ፤ ሪቫይቫል እንዲመጣ እየተጣራን እንዳለን እንዲያውቅልን እናእንዲሰማን ብቻ ካደረግነው፤ እሱ፤ እንደሚሰጠን አምናለሁ።

11 አሁን ፣ ዛሬ ማታ በሌላኛው ማዶ በላይ ባለው፤ የወንድም አውትለው ሕብረት፤ የኢየሱስ ስም ቤተ ክርስቲያን፤ እንሆናለን። ወንድም አውትለው፤ የማምንበት... ሐወርያዊ ቤተክርስትያን፤ ነው። የቤተክርስትያን ስያሜ፤ የኢየሱስን ስም ብሎ የጠራት ይመስለናል። በእምነት ሐዋርያዊ ይመስለኛል። እናም ስለዚህ ዛሬ ማታ እዚያ እንገኛለን። እና እስፓኒሿ ቤተክርስቲያን "አሁን ወደዚያ ኑ፤" እያልን አይደለም፤ ምክንያቱም በሥራ ገበታችሁ ላይ መገኘት ስለሚኖርባችሁ። ከዚያ በኋላ ከሐሙሰ ጀምሮ፤ የክርስትያን ሰራዎች ሰዎች ታላቅ ሰብሰባ ይደረጋል፤ ሐሙስ፤ አገልግሎት በሌሎች አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ካለቀ በኋላ። እናም በሰብሰባው ላይ፤ ጥሩ ጥሩ ተናጋሪዎች ይገኙበታል፤ እነ ኦራል ሮበርትስ፤ በቅርብ የዳኑ አንዳንድ የሜተዲስት ወንድሞች፤ እነሱም ከባድ ተናጋሪ ነው ይሉታል። በኮንፈረንሱ እንደምትደሰቱም እርግጠኛ ነኝ። እናንተ ታዳጊ-ልጆች፤ ወንድማችን ሲያስተዋውቅ እንደነበረ፤ የታዳጊ-ልጆች ክፍለጊዜም ይኖራል። በዚህ ጉዳይ እንዲሳተፉ ልጆቼን አመጣለሁ። እናንተም ጎራ በሉ፤ በደስታ እንቀበላችኋለን። ጌታ ሁላችሁንም ይባርክ።

12 አሁን የተባረኩ ቃላትን ለማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን መክፈት እፈልጋለሁ። ዛሬ ጠዋት፤ ጥቂት ጊዜ ነው፤ ብዙም አላቆያችሁም፤ ይህን ጥቂት አንቀጽ መርጫለሁ፤ አንዱ በአንደኛ ሳሙኤል ውሰጥ ይገኛል፤ ሌላኛው ደግሞ በኢሳይያስ ነው። በመጀመሪያ ከኢሳይያስ ለማንበብ እፈልጋለሁ። እኔም...

13 ሁላችሁም፤ በደንብ ይሰማል አይደል? በማይኮቹ መካከል፤ ለምን እንደሆነ አላውቅም፤ በጣም ሴንሰቲቭ እየመሰሉኝ ነው። እዚያ ያላችሁ ሁሉ ይሰማል፤ እጃችሁን አንሱ። መልካም፤ ጥሩ።

14 አሁን፤ በመጠኑም ቢሆን ጎርነን ብያለሁ፤ በርግጥ፤ ብዙ ከመናገር ነው። ይመስለኛል፤ የዛሬ አስራ ሰድሰት ዓመት፤ ከነዚህ የሰፓኒሽ ወንድሞች ጋር እዚህ ከነበርኩ ወዲህ፤ ምናልባት ወደ አሰራ ሰድሰት ወይም አሰራ ሰባት ዓመታት በፊት፤ እሰከ አሁን ድረስ፤ እሰብካለሁ። ያኔም ቢሆን፤ ደክሞኛል ሰል ነበር፤ አሁንም ደክሞኛል፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ጸጋ እየቀጠልኩ ነው።

15 አሁን ወደ ኢሳይያሰ 40፤ ኢሳይያሰ 40ኛ ምዕራፍ እንሸጋገር፤ እና 1ኛ ምዕራፍ፤ ወይም 1ኛ ሳሙኤል 3ኛው ምዕራፍ። እናም ለቃሉ ንባብ እነዚህ ሰፍራዎች ይዘን ሳለን፤ ለፀሎት አንድ አፍታ ብቻ አንገታችንን ዝቅ እንድናደርግ እፈልጋለሁ።

16 የሰማይ አባታችን፤ ዛሬ በዚህ ውብ መቅደሰ ውሰጥ ለመቆም ስለታደልን እናመሰግናለን ይህ ለእግዚአብሔር እና ለሰራው የተሰጠ ነውና። ባርያዎችህ ከዚህ መድረክ በሰተጀርባ ወይም በዚህ በመድረክ ብዙ ጊዜ እንደቆሙ እናውቃለን፤ ለሰራህ ከተሰጠ ህይወት ጋር።

17 እናም፤ **ይህ** ማለዳ፤ ያኔ የተጀመረውን የሪቫይቫል ትዝታዎችን፤ የቆዩ ትዝታዎች አመጣብን፤ እንደ እሳት ዓምድ፤ እንደ ትልቅ ብርሃን ሆኖ ከወረደው ከመንፈሰ ቅዱስ ጋር፤ መልእክቱ ምድርን እንደሚያዳርሰ ተነገሮ ነበር። እና አሁን ዛሬ ታሪክ ሆኗል። መልእክቱ እነ ኦራል ሮበርትሰ እና ቶሚ ኦሰቦርን ካዩት በኋላ፤ እሳቱ በታላላቅ ሰዎች በኩል ተያይዟል፤ ቶሚ ሂክሰ እና ሌሎችም ብዙዎች። አንድ ላይ ሆነን ባደረግነው የጋራ ጥረት፤ መልእክቱ ከሰማይ በታች ባሉ በሁሉም ሕዝቦች ውሰጥ የጴንጤቆሰት መልእክት፤ የሪቫይቫል እሳት

እንደለኮሰ እናያለን። ኃያል አምላክ ሆይ፤ ስለዚህም ለአንተ ምስጋና እና ክብርን እናቀርባለን።

18 አሁንም ልባችንን እንድታድስልን እንጸልያለን፤ በቅርቡ ለሚከናወነው ታላቅ መነጠቅ ለመዘጋጀት፤ እምነታችን ነውና። ልባችንም ለዚያ ወይም ለሌላ ለእኛ በምታሰቀምጠው ለማንኛውም ነገር ሁኔታ የተስተካከለ ካልሆነ፤ ድክመቶቻችንን ይቅር እንድትለን፤ ዛሬም በቃልህ እንድትናገረን እንለምናለን። የዚህን ቤተክርስቲያን ፓስተር ፣ ዲያቆናትን ፣ ባለአደራዎችን እና ምእመናንን፤ አባላትም ሁሉ ባርክልን። ይህች ታናሽ ኳየር፣ ፒያኒስቱ፣ ሙዚቀኞቹ ሁሉ ባርካቸው። የዚህን ቤት ደጆች የረገጡትን ሁሉ፤ በአንድነት ባርካቸው። በየጊዜው እየተለወጡ መውጣት ይሁን፤ ገና ሲገቡ ከነበሩበት ይልቅ ወደ አንተ የተጠጉ ይሁኑ። አድርግልን፤ አባት ሆይ። ልመናችን በኢየሱስ ስም ነውና፤ በዚህች ማለዳም፤ ይህ ይሁን። አሜን።

19 አሁን ወደ ኢሳያስ 40ኛው ምዕራፍ ሄደን፤ እናነባለን።

> **አጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ፥ ይላል... አምላካችሁ።**
>
> መልካም ቃላትን **ለኢየሩሳሌም ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት እንደ ተፈጸመ፥ ኃጢአትዋም እንደ ተሰረየ፥ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ... ሁለት እጥፍ እንደ** ተቀበለች **ወደ እርስዋ ጩኹ።**
>
> **በበረሃ የሚጮህ የእዋጅ ነጋሪ ቃል፤ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።**
>
> **ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ጠማማውም ይቃናል፥ ሰርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል፤**
>
> **የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን** ተናግሮአልና።

አሁን በሳሙኤል መጽሀፍ፤ አንደኛው ሳሙኤል፤ 3ኛ ምዕራፍ፤ 1ኛ፣ 2ኛ፣ እና 19ኛ ቁጥር አነባለሁ;

> **ብላቴናውም ሳሙኤል በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፤ በዚያም ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ፤ ራእይም አይገለጥም ነበር።**
>
> **በዚያም ዘመን እንዲህ ሆነ፤ ዔሊም በስፍራው ተኝቶ ሳለ፡ የዔሊዓይኖች ማየት እስኪሳናቸው ድረስ መፍዘዝ ጀምረው ነበር።**
>
> **... የእግዚአብሔር መብራት ገና ሳይጠፋ፥ ሳሙኤልም የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት በእግዚአብሔር መቅደስ ተኝቶ ሳለ፥**
>
> **እግዚአብሔር ጠራው፤ እርሱም... እነሆኝ አለ።**

19ኛው ቁጥር;

**ሳሙኤልም አደገ፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፤ ከቃሉም እንዳች በምድር ላይ አይወድቀም ነበር።**

20 ኦህ፤ ይህ ርዕስ እዚህ አንድ ወር ሙሉ ልንናገርበት የሚያስችል በቂ ርዕስ ነው፤ ከዚህ ታላቅ ርዕስ እጅግ ብዙ ሐሳቦችን ማውጣት ይቻላል። በዚህ ማለዳ ግን፤ ደግሞም በ… በትክክለኛው ጊዜአችን ለመውጣት ያለን ሀያ ደቂቃ ብቻ ነው። ስንደይ ስኩል ያለቀ ይመስለኛል ወይም ቀጥሎ ይሆናል፤ አላውቅም። ምንም ይሁን፤ ግን፤ **የእግዚአብሔር ድምጽ በነዚህ የመጨረሻ ቀናት፡** የሚል ርዕስ መጠቀም እፈልጋለሁ።

21 እጅግ ድንቅ ጊዜ ይሆናል። ከተናገርነው ቅዱስ ቃል እንዳስተዋልነው፤ "በሳሙኤል ዘመን ራእይም አይገለጥም ነበር" ይላል። ስለዚህ፤ "ራእይ በሌለበት፤" መጽሓፍ፤ "ህዝብ ይጠፋል" ይላል። ራእይ ሊኖር ይገባል። ራእይም ወደ ነብያት ይመጣል፤ ይህም ለእነሱ የሚነገር የእግዚአብሔር ቃል ነው።

22 እንደተረዳነውም ዔሊ ነብዩ አልነበረም፤ ዔሊ ካህን ነው። ስለ እረጀም፤ አይኖቹ ደክመው፤ ከቦታ ቦታ ለመሄድ ማየት የተሳነው፤ በጣም ግዙፍ ሰው ሆኗል። የእግዚአብሔርም ስራዎች ሳይሰራ መቅረት ጀማምሮታል።

23 ይህም ልክ አሁን እንዳለ ዓይነት ነገር ነው። እንደሚመስለኝ ቤተክርስትያን፤ ድርጅቲቱ እና ተቋሞች፤ ለዘመናት በስራው ላይ ስለቆዩ፤ እንዝህላል መሆን ጀማምሯቸዋል። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ስራ፤ የእውነት ቃል፤ ሳይሰራ ቀርቷል፤ ምክንያቱ ቤተክርስትያን፤ በራሷ፤ ማየት-የተሳናት ሆናለች። ስለዚህ ዛሬ፤ የእግዚአብሔር ድምጽ፤ በመካከላችን እንዲናገረንና፤ እንዲመልሰን ያስፈልገናል።

24 አያችሁ፤ ዔሊም፤ ተኝቷል፤ ዓይኖቹም… መደከም ጀምሯል። ዔሊ ካህን ነበር። ከጌታ ግልጽ የሆነ ራእይ አልነበረም። ስለዚህ ይህ ታላቅ መጠማት!

25 እግዚአብሄርም የዘመኑን ጥያቄ ለመመለስ ቃል ገብቷል። ሁሌም የሚያደርገው ይህ ነው። ለእኛም የዘመኑን ጥያቄ ለመመለስ፤ አሁን እየኖርንበት ያለውን ጊዜ ለመጋፈጥ፤ ዛሬ የእግዚአብሔር ድምጽ ያስፈልገናል። እናም ቃል ከገባ በኋላ፤ ቃሉን ይጠብቃል ብለን ማረፍ አለብን። አማኞች በፈጣሪአቸው ዘንድ ያላቸው ኮንፊደንስ፤ የገባውን ቃል እንደሚፈጽም ነው።

26 ስለዚህ፤ ዛሬ፤ ቤተክርስትያን ባለችበት ሁኔታ እንድትሆን ያደረጋት አንድ ምክንያት፤ ብዙ ዓይነት ድምጾች ስላሉ ነው፤ ቤተክርስትያን ከእግዚአብሔር ድምጽ ለይቶ የሚያማልላት፤ ሌላ ብዙ ድምጽ ስላለ ነው፤ ብዙዎች የእግዚአብሔር ድምጽ በመካከላቸው እንኳን ቢነገር እጅግ እስኪጠራጠሩ ድረስ። እረ እንደው እንግዳ ነገር ስለሚሆንባቸው፤ በጭራሽ አይረዱትም። እራሳቸውን በዘመኑ ድምጽ እጅግ አብዝተው አሰወሰደዋል!

27 ቃሉን ስናነብ፤ ካስተዋልነው፤ የእግዚአብሔር ድምጽ እንግዳ ነገር ሆኖባቸው ነበር።

28 ዛሬም እንደገና… ብዙ ሌሎች ድምጾች ስላሉ፤ ይህ የእግዚአብሔር ድምጽ እንዲሁ ሆኗል። እግዚአብሔር ይህን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶ፤ ሌሎች ድምጾች ግን የእግዚአብሔርን ድምጽ ከተቃረኑ፤ እንግዲያውስ የእግዚአብሔር

ድምጽ ሲነገር እንዳናስተውልና፤ ግራ ሊያጋባን፤ የጠላታችን ድምጽ መሆን አለበት።

29 በዔሊ እና በሳሙኤል መካከል የነበረ ነገርም እንዲህ መመሳሰል እንዳለው እንረዳለን። ዔሊ ወድያው የእግዚአብሔር እንደሆነ አውቆታል። እና ይህ ለዔሊ ፍጹም—ውርዴት ነው። ምክንያቱ፤ የእግዚአብሔር ድምጽ፤ ለሳሙኤል ሲነግረው፤ የዔሊን ጥፋቶች ሁሉ ዘርዝሮለታል፤ ልጆቹ፤ ከመስውያው ገንዘብ እና—ስጋ እየወሰዱ፤ ልጆቹን እሹሩሩ ብሏቸዋልና። ይህ ልክ አልነበረም። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ቃል የሚጻረር፤ ድርጊቶችን ሲያደርጉ ነበር።

30 ሳሙኤልም... ሳሙኤል ማድረግ የሚገባው፤ እቅጯን መናገር ብቻ ነው። ያድግበት ዘንድ የሄደበትን ሰፋራ የሚጻረር ስለነበረ ግን፡ይህ ለማድረግ ትንሽ ዘግየት ብሏል። ዔሊም በቤተመቅደስ። ዔሊም፤ “ተናገር” አለው። አያችሁ? እና ምን ሊሆን እንደሆነም እቅጩን ነግሮታል፤ የሳሙኤል... ማለት፤ “የዔሊ የክህነት ዘመን፤ እንዳበቃለት፤” እግዚአብሔር ነግሮታል፤ እግዚአብሔር መልእክቱን በነቢዩው በሳሙኤል ሲያስተላልፍ ነበር። ከልጅነት ለጌታ የተሰጠ፤ ያልተለመደ አወላለድ። ገና ህጻን ልጅ ሳለ፤ እግዚአብሔር አነጋገረው፤ ወደፊት ለሚጠብቀው ሥራ ሰያዘጋጀው ነበር። የዔሊም ጊዜ እየተጠናቀቀ ነበር።

31 ዛሬም በምድር ብዙ ዓይነት ድምጾች አሉ፤ ይህም መለኮታዊ ድምጽ ስለሚያደነዝዝ፤ እጅግ ከባድ ነገር ነው። ብዙ የእውቀት ድምጾች፣ ብዙ የአዋቂዎች እና የታላላቅ ሰዎች ድምጾች አሉ፤ ያውም፤ በአእምሮ ብቃታቸው፤ አሕዛብን የሚያንቀጠቅጡ። የአንዲት ሌሊት-ሰዎች አይደሉም፤ ሕዝብን የሚያንቀጠቅጡ፤ ታላላቅ ድርጅቶችን አንድ ማድረግ የሚችሉ ናቸው፤ ለሰው ግራ ይጋባል። አበባ የተዋሉ፤ ታላላቅ ስብሰባዎች። በሚያበለጽጉ ነገሮች እና በአካሄቸው ግራ ለመጋባት፤ በቂ ናቸው። እነዚህንም የሚያደርጉ እና—የሚያጎሉ ድምጾችም አሉ። ስለዚህ የጌታን ድምጽ፣ እውነተኛውን የእግዚብሔር ድምጽ፤ ገለል ያደርጋል።

32 “የእግዚአብሔር ድምጽ፤” “የጌታ ድምጽ መሆኑ እንዴት እናውቃለን? ” ይላሉ። ምክንያቱ፤ ያኔ ለምልክት ማረጋገጫ ያለው ነብዩ ነበር። በዚህ ዘመን ግን... አሁን ዛሬ፤ የጌታ ድምጽ መሆኑስ፤ እንዴት እንለያለን፤ የነብዩ ቃል ማረጋገጫ ስለሆነ። የእግዚአብሔር ነብዩ እንዲህ ነው። እውነተኛ የእግዚአብሔር ድምጽ ብቻ ወደ ትክክለኛና፣ ህያው፣ መለኮታዊ አምላክ ይመልሳቿል፤ መለኮታዊ ቃል ጋር፤ ከቃሉ መለኮታዊ ማረጋገጫ ጋር። የእግዚአብሔር ድምጽ መሆኑን የምናውቀው ያኔ ነው። ምክንያቱም ፣ መለኮታዊውን... በሌላኛው አድማስ፤ ይሄንን የሚያደነዝዝ ብዙ ነገር አለ። ግን፤ አስታውሱ፤ ወደፊት ይወጣል! ይደምቃል፣ ደግሞም ይሆናል።

33 በፖለቲካው ዓለም ውስጥ፤ አንድ ድምጽ አለ። ታላቅ ድምፅ ነው። ሰዎችም፤ የፖለቲካው ታላቁ ቀን... በአብያተ ክርስቲያኖቻቸው እና በሁሉም ነገራቸው፤ ፈጽሞ፤ ይቀላቀልባቸዋል። እና አብዛኛው ጊዜ፤ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፤ የፖለቲካው ድምጽ ቸርቾች ውስጥ ካለው የጌታ ድምጽ ይልቅ ጠንካራ ነው፤ ባይሆን’ማ የአሜሪካ ህዝብ የዳረጉት ነገር

ባላደረጉ ነበር። አያችሁ? በፍጹም አያደርጉም ነበር። የእግዚአብሄር ድምጽ በቤተክርትያን ህያው ሆኖ ቢጠበቅ ኖሮ፤ ያንን ስሕተት አያደርጉም ነበር። ነገር ግን ዛሬ በምድር ላይ ከእግዚአብሄር ድምጽ ይልቅ የፖለቲካው ድምጽ፤ ሰዎች ለአንጋፋነት፤ ለእውቀትና፤ ለፖለቲካ ሰልጣን ብለው፤ የክርሰትና ብኩርናቸው እስኪሸጡ ድረስ እየበረታ ነው። ይሄን ማየት ውርዴት ነው። አገራችን ከተሰራችበት፤ ከተገነባችበት ዋና ነገር፤ ህዝቡ ወደ ኋላው ተመልሶ—ለሌላው ሀገር የጣልነው ነገር መረጠ። እናም—ከእነ ፕለይማውዝ ሮክ፤ **ከመይፍላወር** ወዘተ፤ ወደዚህ ደርሰን—ይህ አሁን የያዝነው ታላቅ ኢኮኖሚ አደረሰን። እኛ እራሳችን ነጻ ለመውጣት እጅግ ወደ ታገልነው ነገር፤ ወደ ማሰርያው ተመለሰን፤ መጽሓፍ ቅዱሰም እንዲህ እንደሚሆን ተናግሯልና።

34 እናም፤ ከነቢዪ ይልቅ ክህነት የነበረው የዔሊ ሰርዓት። ነቢዪ ቃል ነው። ካህኑ ደግሞ ቤተክርሰቲያን ነበር።

35 ቃሉ ለሕዝቡ እንግዳ እሰኪሆንባቸው ተራ እሰኪሆንባቸው ድረሰ ወደዚህ ደረጃ ወረደ። አይገባቸውም። ከሱ ጋር ልምምድ ሰለሌላቸው፤ ቃሉን ትናገራቸዋለህ፤ አያሰተውሉትም። ጳውሎሰ “መለከት እርግጠኛ ያልሆነ ድምፅ ከሰጠ፤ ራሱን ለጦርነት ለማዘጋጀት ማን እውቀት ሊኖረው ይችላል?” አለ።

36 ህዝቡ የተለማመደው የ—የ—የ ቤተ ክርሰቲያን ድምፅ፤ የቤተ ክርሰቲያን መለከት ነው፤ “እኛ የሰንበት ትምህርት ከሌሎች ይልቅ የተሻለ ነው።” ይሄ ትርጉም የለውም። “ለሌሎች ካላቸው ይልቅ፤ በእኛ ተቋም ብዙ ነገር አለን። እኛኮ በሐይማኖት ተቋማት መካከል ትልቁ ነን።” ተመልከቱ፤ ሰዎች የተለማመዱት የድምፅ ዓይነት ይህ ነው። ሰዎችን ለማጥመድ እና ወደነሱ ለማሰገባት፤ ጎዳና ይወጣሉ። በታላላቅ ኮንፈረንሶች፤ በአሰር ሺዎች ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ ያሰገቧቸዋል። ፍላጎታቸው ምንድነው? “ትልቁን ቤተክርሰቲያን አለን። ትልቁ ጉባኤ እኛ ነን። ብዙ-አባላት ያሉት የሰንበት ትምህርት የእኛ ነው። የከተማው ከንቲባ በኛ ቤተክርሰትያን አለ።” ያ ሁሉ ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ ግን ያች ቤተክርሰቲያን ለአምላክ ድምፅ፣ ለወንጌል መለከት ካልሰለጠነች፤ ምን መልካም ነገር ያሰገኛል?

37 በመንግሰታችን የተከሰተው ነገር እንደተነሳ አንድ ነገር ሲነሳ፤ ምን ይሆናል? ቤተክርሰቲያን የመለከቱን ድምጽ አታውቅም፤ እነሱም ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። ታላቁ የብልፅግና ተሰፋ፤ ግዙፍ ዕውቀት እየመጣ ነው፤ እነሱም መጽሓፍ ቅዱሰ አሰቀድሞ ወደተነበየው ወደ ዋናው ይሄዳሉ፤ ደግሞም ያሰገቡታል። አያችሁ፤ የፖለቲካ ድምጽ! እናም የሀይማኖት ድምጽ፤ የወንጌሉን ድምጽ እንደሚረግጥ የታወቀ ነው፤ ባይሆን ኖሮ ግን ያደረጉት ነገር ማድረግ ባልቻሉ። ምክንያቱም እኛ ብዙ ቃል ተገብቶልናል፤ ብልጽግና ቃል ተገብቶልናል፤ ደግሞም እንደምናገኘው ምንም አያጠራጥርም።

38 አሁንም ግን፤ ያ ለአማኝ፤ ምንም ማለት አይደለም። በዕብራውያን መጽሐፍ ውሰጥ እንሂድ፤ 11ኛው ምዕራፍ ላይ፤ ቅዱሰ ጳውሎሰ፤ በዚያ ዘመን፤ እንዴት፤ “ሰፍራ ሳይኖራቸው፤ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው እንደዞሩ፤ እና ከተማይቱን እንዳላገኟት” ይናገራል።

39 ከክርስቶስ ሞት ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ፤ በኒቂያ፣ በሮም፤ በታላቁ የኒቂያ ጉባኤ፤ የተነሱ ታላላቆቹ ጉዳዮች በተመለከተ እያነበብኩ። ያኔ ለእውነት የቆመችው ታላቋ ማሕበር ላይ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስፈልጋቸው። ወደ መጀመርያዋ ቤተክርስትያን የተቀላቀሉ ሮማውያን አማኞች ዶግማዎችን ቀላቀሉባት፤ለምሳሌ፤ ክሪስማስን መጥቀስ እንችላለን።

40 ክርስቶስ፤ በታህሳስ ወር ሃያ-አምስተኛው ቀን በክሪስማስ አልተወለደም—እኔም ብሆን። ለምን፤ የይሁዳ ተራሮች በረዷማ ስለሚሆኑ፤ በተጨማሪም... የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶችን ይጻረራል። የበግ ጠቦቶች በሚወለዱበት፤ በጸደይ ወቅት ነው የተወለደው።በቤት ይልቅ በበረት ለምን ተወለደ? ጠቦት ስለሆነ ነው። ለምን በሚስማር ተቸንክሮ ወደ ተሰቀለበት ወደ መሠውያው አልሮጠም? ወደ መሰቀል ስለተመራ ነው። በግን ወደ መታረድ ይነዳል። እሱም የበግ ጠቦት ነበር። ሲወለድም በጎች በሚወለዱበት ወቅት ነው።

41 አያችሁ፤ እነሱ ግን፤ ይህ የሚያደርጉት፤ በሰርዓተ ጸሐይ መሰረት የሚከበር፤ የጸሀይ-አማልክት፤ የልደት ቀን ነበራቸው፤ ከታህሳስ ሀያኛው ቀን እስከ ሐያ-አምስተኛው ቀን ባሉ አምስት ቀናት—ጸሀይ፤ ጸሐይ፤ እምብዛም የማትንቀሳቀስበት ጊዜ አለ። በሐምሌ ወር ረጅሙን ቀን እስኪመዘገብ ድረስ፤—በየቀኑ በትንሽ በትንሹ ይራራቃል፤ ቀኑም እየረዘመ እየረዘመ ይሄዳል። ከዚያ በኋላ፤ በታህሳስ ውስጥ፤ ቀኑ ያጥራል። እናም ከዚያ በኋላ፤ አጭሯ የሀያ-አምስተኛዋ ቀን፤ ከሀያኛው እስከ ሀያ-አምስት ቀን፤ የሮማውያን የሰርከስ ክብረ በዓል እና የጸሐይ-አምላክ ልደት ይከበርበታል። ከዛ በኋላ፤ የሮማውያንን አምላክ ጁፒተርን፤ እንዲህ በማለት፤ ማስተዋወቅ ጀመሩ፤ “የእግዚአብሄር ልጅን እና የጸሀይ-አምላክ የልደት ቀን እንውሰድና፤ አንድ ላይ ቀላቅለን ታልቅ ክብረ በዓል እናደርገዋለን” አሉ። ይህ ተቃርኖ ነው! እና፤ ኦህህ ፣ በዚያ ውስጥ የጨመሩት መርዝ ብዛቱ!

42 ከቃሉ ጋር መወገን የፈለጉ እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች፤ እነ ፖሊካርፕ ፣ አይሪንየስ ፣ ማርቲን ፣ እነዚያ ታላላቅ ፣ ቀደምት ፣ ከእውነት ጋር መቆየት የሚፈልጉ ቅዱሳን ሰዎች... ወደ ኒቂያ ጉባኤ ሲያመጧቸው፤ አንዳንዶቹ እጅግ ተቃውሞ ደርሶባቿል ጉባኤውን ለመካፈል ልብስ ሳይለብሱ አንድ የበግ ቆዳ ብቻ ለብሰው ነብያቶች ከበረሃ እስከመምጣት ደረሱ። የጌታን ቃል እያወቁ። ታዋቂ ለመሆን፤ አሥራ አምስቱ ደም አፍሳሽ የፖለቲካ ቀናት፤ አሳለፉ። ከዚያ በኋላ አንድ ሺህ የጨለማ ዓመታት አሳለፍን፤ አያችሁ።

43 እግዚአብሔር ግን ያንን የመለከት ድምጽ ዳግም እንደሚሰማ ቃል ገብቷል። ሰዎች ትክክለኛውን የቃል ድምጽ ሁልጊዜ ይሰሙታል፤ የምታደርጉት ሁሉ በቃል መርምራችሁ ይሁን።

44 የፖለቲካ ድምፅ። ዛሬ በአሜሪካ እና በተቀረው ዓለም ውስጥ፤ በከፍተኛ ደረጃ የሚሰማ ድምጽ አለ፤ ይህም ድምጽ የሆሊውድ ድምፅ ነው። ዓለምን አጥምዷታል። ብቻ አንድ ሰው በሆሊውድ ውስጥ የሆነ ነገር ይዞ ይምጣ፤ በመላው አገሪቱ ታገኙታላችሁ። አሁን፤ ሴቶቻችን ላይ፤ የአለባበስ፣ የፀጉር አሠራር፤ ንድፍ እንዳስቀመጡ አይተናል። ያንን አለባበስ ፈብርኳል።

45 እዚህላይ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ መለየት አለባት! ሌሎችን እንደምሳሌ፤ ስለምታዩ ግን፤ ብዙ ግራ መጋባት አለ። ጠፊ ስለሆነ፤ እራሳችሁን በእንደዚህ ዓይነት ምሳሌ በጭራሽ አትስሩ። ሁል ጊዜ፤ ስለሱ የሚለውን፤ የእግዚአብሔርን ድምፅ ብቻ ስሙ።

46 እናም በሆሊውድ፤ ነገሮች እጅግ ሲጋነን እናስተውላለን። ከመቀጠላችን በፊት በዚህ ጉዳይ ላይ ለአፍታ ያህል ልናገር። አንድ ነበር—አንድ ነገር በቅርብ ጊዜ የወጣ ነገር፤ አንድ ሰው—በሆሊውድ… ሰውየውን ለመቃወም አይደለም፤ ክርስቶስ የሞተላት ሟች ሰው ነው፤ እናንተን ለማስረዳት ግን። ልጆች "ሁላ-ሁፕ፡" ሁላ-ሁፕ፤ ወይም የሆነ ነገር ብለው የሚጠሩት፤ አንድ ነገር ፈለሰፉ። ይሄን ተከትሎ፤ በሕጻናት ላይ የሚመጡ ብልግናዎችን፤ እና ነገሮችን ካስተዋላችሁ። ልክ አይደለም።

47 አሁን፤ ሆሊዉድ በ—በታጠቂ ተሞልታለች። አሁን ታሪክን የሚያውቅ ሰው፤ በድሮ ዘመን በዚያ የነበሩ ሰዎች፤ እንደ ሌላው ህዝብ፤ የተረጋጉ ዜጎች—ሳይሆኑ፤ ይትጥቅ ተዋጊ መሆናቸውን ያውቃል። አመጸኞች ነበሩ፤ እንደነ አል ካፖን እና ዲሊንገር የመሳሰሉ ናቸው። በቴሌቪዥን ስርጭት ላይ፤ "ገንሰሞክ" ብለው የሚጠሩት—የሆሊውድ ጨዋታ አላቸው። በቀደምለት፤ **ከሞኒተር** የሰማሁት ነው፤ ይሄን የሚጫወተው ሰውየ፤ አርነስ ወይም ሌላ፤ አርነስ፤ ወይም ሰሙ ማን እንደነበረ ረሳሁ፤ ያንን የሚመራው እሱ ነው… በካንሳስ የፖሊስ አዛዥ የነበረ የማት ዲለን ገጸ ባህርይ ነው። ማት ዲለን ማለት እንደ ጥንቸል ቢጫ የሆነ ሰው ነበር። ከዶጅ ከተማ ወደ ውጪ ወጥቶ በጫካ ውስጥ እየጠበቀ፤ ሀያ-ሰምንት ንጹሀን ሰዎችን፤ ከበስተጀርባቸው በጥይት መትቷል። እናም ሰው ሲመጣ አንድ ሌላ ሰው ይጠራውና አደገኛ ሰው እየመጣነው ብሎ ይነግረዋል፣ ከዛ ይጠብቀውና፤ ሰውየው ሲገባ፤ ከበስተጀርባው ይተኩስበታል። አሁን ይህ ሰው "ሽፍታ" እንደሆነ አውቀናል። ታድያ፤ ይሄ'ኮ—ይሄ'ኮ ፍጹም ሐጥያትን ማቆለጳጰስ ነው። ቢሆንም የአገራችን ህጻናት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚሉት ይልቅ ስለ ማት ዲለን የሚያወሩት ይበዛል። መ—መ—መደብሮች፤ የልብስ አምራቾች የአስር-ሳንቲም መደብሮች ሁሉ፤ ትንንሽ—አሻንጉሊት ጠመንጃዎች አንጠልጥለዋል፣ የትም መግዛት የምትችሏቸው—ትንንሽ ባርኔጣዎች ጋር። ይሁን መልበሱ ችግር የለውም፣ እኔ—እኔ ግን ነገርኳችሁ፤ አያችሁ። ከዛ በኋላ—እነሱ፤ የንግዱ ዓለም፤ ያ ነገር ተጠቅመው ሚሊዮን ዶላሮች ያተርፍበታል።

48 "ቅዱስ ፓትሪክ ቀን" ብለን የምንጠራው፤ "ሃይማኖታዊ በዓላት" የምንላቸው አሉ። የንግዱም ዓለም ይሄን ይወስድና፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮችን ያተርፍበታል። "የእናቶች ቀን" ብዙ አበባ። ለምን፤ እናትኮ ቀን ሁሉ የተከበረ ሊሆንላት ይገባል። በሆነ ቦታ ደክማ፤ አርጅታ ከሆነች፤ ሂድ እና ጎብኛት። ከምትልክላት አበባ ወይም ከሌላ ሁሉ ይልቅ የበለጠ ዋጋ አለው። አያችሁ፤ ይለቃቅሙታል። ድምጽ ነዋ፤ እና—እኛም እንቀያይጠዋለን። ይህ በእውነት ልክ አይደለም። ግን ምንስ ታደርጉታላችሁ? አያችሁ፤ እኛኮ—እንደው እኛ…

49 እኔ—እኔ የማምንበት፤ አንዳች ነገር እንድነግራችሁ ወደ አንድ ነጥብ ለመምጣት እየሞከርኩ ነው። የጌታ ድምፅ፤ ድምጹ ብርቅ ነው።

50 አሁንማ፤ ርቀቱን አስፍተውታል። አስተውላችኋል? ወጣቶቻችን “ሪኪ” እና “ኤልቪስ” እየሆኑ ናቸው። በዚህ ስም የተሰየመ ልጅ ካላችሁ፤ በፍጥነት ቀይሩት፤ ቁጥር “አንድ” ወይም “ሁለት፣” ወይም ሌላ ነገር በሉት። ይሄን ስቅጣጭ... በጭራሽ፤ “ስሙ ምን ልዩነት ይፈጥራል?” ትላላችሁ፤ ለምን፤ በርግጥ፤ ትርጉም አለው። ስምህ ሕይወትህን ያስረዳል። “ወንድም ብራንሃም፤ አሁን፤ ስነ ቁጥር ላይ ገባህ።” አይ፤ አልገባሁም! ጌታ ስራዊት እንዲህ ይላል ላይ ነኝ! ስሙ ያዕቆብ በነበረ ጊዜ፤ ያዕቆብ ለተባለ ሰሙ፤ እንደ— እንደ አታላይ፤ እንደ ነጣቂ፤ ኖሯል። እግዚአብሔርም እሱን ሲቀይረው፤ ስሙን ለወጠለት። እግዚአብሔር ሳኦልን ወደ ጳውሎስ፣ ስምዖንን ወደ ጴጥሮስ ቀየረ። በእርግጠኝነት ትርጉም አለው። እነ ሪኪ እና ኤልቪስ እና እንደዚህ ያሉ ስሞች፤ ልጆችን በቀጥታ ወደዚያ የሚወረውር ዘመናዊው የአሜሪካ ስም ነው። አያችሁ ምን ማለቴ እንደሆነ?

51 አሁን ይሄን ነገር፤ ደገፍ በማድረግ በዚህ ርዕስ ርቄ ላለመሄድ፤ ተስፋ አደርጋለሁ... (አያችሁ ምን ማለቴ እንደሆነ?) ይሄ ነገር አትረዱትም።እነዚህ ነገሮች ተራ ሰው አይገቡትም። አይገባቸውም፤ ምክንያቱ የተለመዱት አካሄድ ስላላቸው ነው። የሚያደምጡት፤ እነኚህ ድምጾች ናቸው።

52 ተስፋ የሚሰጥ፤ ርቀት ግን የማያስኬድ፤ የፈላስፎች ድምጽ አለ፣ ጸንተው የማይቆዩበት ተስፋ የሚገባ፤ የኮሚኒዝም አለ። ከአሜሪካ ህዝብ መካከል አንድ መቶኛ የሚሆነው በኮሚኒዝም ውስጥ ተጠምዷል። አሁን፤ በኮሚኒዝም ነበርኩ፤ በጀርመን በርሊን ምስራቅ በኩል በኮሚኒዝም ዞኖች ሄጄ ነበር። ውጭ ውጭውን ለማሳየት ትላልቅ ቤቶች አሉ። ውስጥ በእግር ዘለቅ ስትሉ ግን፤ ገና እንኳን ያላለቁ ናቸው። የውሸት ኢኮኖሚ ነው፤ የሆነ ነገር ለመግፋት እየሞከሩ ነው።

53 እናም፤ ኮሚኒዝም በተወለደበት፤ በሩስያ... ከዓመታት በፊት፤ ወጣት ሰባኪ በነበርኩበት ጊዜ፤ ከሠላሳ-ሦስት ዓመታት በፊት፤ እነ ናዚዝም፣ ፋሺዝም፤ እና ኮሚኒዝም እያደጉ በነበሩ ጊዜ፤ “ሁሉም በኮሚኒዝም ሁሉንም ይውጣል ብያለሁ በጌታ ስም! ተናግሬአለሁ።” ከተጠቀምንበት ግን፤ እግዚአብሔር መውጫ መንገድ እንደተወልን፤ አስተውላችኋል። በሩሲያ አንድ መቶኛ ብቻ ናቸው ኮሚኒስት፤ አንድ በመቶ፤ እነሱ ግን ገዢ መደብ ናቸው። ኮሙኒዝም አንድ በመቶ... ሩስያ አንድ በመቶ ኮሚኒዝም ናት፤ የሚገዟት ን፤ እነሱ ናቸው።

54 በተመሳሳይ መልኩ፤ ሆሊውድ አንዲት ቦታ ናት፤ ግን ገዢዎች ናቸው።

55 የአሜሪካ ህዝብ አንድ ሦስተኛ ወይም ሁለት ሦስተኛ ያህል የሚሆነው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄያጅ ነው፤ የቤተክርስቲያን አባላትም ናቸው፤ በነዚህ ተቋሞች የሚገዙ ግን እነሱ ናቸው።

56 በዚህ ላይ ኮሚኒዝም የሚያስፈልገው የእግዚአብሔር ድምፅ በመካከላቸው ቢነሳ፤ እፍረት ያከናንበዋል።

57 በፊንላንድ ያን ህጻን ልጅ በዚያ ቀን ከሞት ሲነሳ። ይህ ህጻን፤ ከሞት ከተነሣበት፤ ሶስት ስኴር ርቀት እያመጡኝ; ሩሲያውያን፤ ኮሚኒስት ወታደሮች፤ እንባቸው በጉንጮቻቸው እየፈሰሰ፤ በሩስያ ሰላምታ ቆመው። “ሙታንን ሊያስነሳ የሚችል አምላክ እኛም እንቀበላለን” አሉ። ይህ'ኮ የካቶሊክ ቤተ

ክርስቲያን እና የሉተራን ቤተ ክርስቲያን፣ የቤተ እምነቶች ሁሉ እንዝህላልነት ነው፤ ህዝቡን አንዳች ነገር ሳይሰጡ፤ ገንዘብን ሁሉ ወሰደው፤ ድርጅቶች ይገነባሉ፤ ። እንደ ተራው ሰው ይኖራሉ። ይህ ነገር...

58 ሩሲያን የሚያስፈልጋት የጌታ ቃል ይዞ ወደ ሁኔታዋ የሚመጣ ነብዪ ነው፣ ያ ነው—እፍን ማዘጋት የሚችለው። ከዚያ በኋላ ዘጠና በመቶው ያሸንፋል።

59 አሜሪካ የሚያስፈልጋት ሆሊውድን ቆሞ ማውገዝ የሚችል የእግዚአብሔር ነቢይ ድምፅ ነው፤ እነዚህን ነገሮችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ያወግዛቸዋል፣ ከዛ በኋላም የመንፈስ ቅዱሷ ቤተክርስቲያን ታሸንፋለች። የሚቃረኑት እጅግ ብዙ ተጻራሪ ድምጾች፤ እያችሁ፤ ብዙ ግራ መጋባት።

60 የእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን፤ ድምጽ፤ ተጨማሪ አባላት ፍለጋ ነው። ባፕቲስት ሁሉን ትፈልጋለች፣ ሜቶዲስት ሁሉንም ይፈልጋል፤ ፕሬስባይቴሪያን። ሁላችንም እነዚህ አሉብን። ካቶሊኮችማ እንዳለ ለመጠቅለል የፈለገ ይመስላል፤ ደግሞም ያደርጉታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ድምፅ ነው። ይገዛሉ።

61 ልዑል እግዚአብሔር ግን በመጨረሻ ይገዛል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል ግን፤ አንድ ቀን፤ ቅዱሳን ያሸንፋሉ። ያሸንፋሉ።

62 ብዙ አስከፊ ድምፆች! ሌላው የሐሰተኛው ነቢይ ድምፅ ድግሞ አለ። እራሱን ነቢይ ብሎ የሚጠራ፤ ሰቅጣጭ ድምፅ ያለው ሰው። ነቢዪ፤ ማለትኮ፤ ሰባኪ ነው። በዘመናዊው ቃል "ነብይ" ማለት በትክክል "በመገለጥ የሚሰብክ ሰው ማለት ነው።" የእግዚአብሔርን ቃል እየካደ፤ የእግዚአብሔር እውነት እየካደ፤ ሽንጡን ገትሮ ነቢዪ ነኝ የሚል፤ ሰው አለ። ብዙ ድምፆች አሉ!

63 ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፤ ወደዚህ እንደምመጣ የመራኝ አንድ ወንድም እዚያ ነበር፤ እና... ለምን በጎዳናው ወደላይ ዞሬ ወደዚህ እንደተመለስኩ የገረመው ይመስለኛል። ጥቁር ጓደኞችን—ኔግሮ ነው። ወንድማችን፤ እዚህ ከሆንክ፤ የሆነ ነገር እያዳመጥኩ ስለነበረ ነው። "መሐመዱ ኤልያስ፤" ወይም የሆነ፤ "ወጣቱ መሐመድ ኤልያስ" ብለው የሚጠሩት፤ እዚህ ቤተመቅደስ አላቸው። ከሆነ ድምጽ ጋር አድገው፤ ድምጹ እነሱ እንደሆኑ ይናገራሉ ይህም የጥቁር ዘርን—ከዚህ አስከፊ ሁኔታ ለማውጣት ነው። ያንን፤ እያችሁ፤ ዋናው፤ የነሱ—የነሱ—ሙስሊም እዚህ ነው፤ መስጊዳቸው። ለምን፤ አይታያችሁም፤ ዋና ዳራው፤ የተሳሳተ ነው!

64 እናንተ ጥቁር ሰዎች፤ እንደ ነጮች፤ እንደ ቡኒ ሰዎች፤ እና እንደ ቢጫ ሰዎች፤ ወደ ሞ-... በሙሐመዳዊነት አትወሰዱ፤ ወደ ዋናው መጽሓፍ ቅዱስ ሰርዓቶች ተመለሱ፤ ወደ ክርስቶስ ተመለሱ። መሐመዳዊነት የቃል ተቃዋሚ ነው። በደቡብ አፍሪካ ደርባን ውስጥ፤ ሳለን፤ በአንድ ጊዜ አሥር ሺህ መሐመዳውያንን ወደ ክርስቶስ የማምጣት አጋጣሚ ነበረኝ። ከሥነ-ልቦና ሌላ ፍሬ የለውም። በርግጥ ሥነ-ልቦና ቃሉን ካልካደ ሥነ-ልቦናም ችግር የለውም። ሥነ-ልቦና ቃሉን ሲክድ ግን፤ የማይታወቅ ድምፅ ይሰጣል። ሥነ-ልቦና ስሕተት ነው። ከእግዚአብሄር ቃል በቀር፤ ሁሉም ያልፋል ብሎ፤ ኢየሱስ የተናገረው ነገር አለ፤ "ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።" ስለዚህ፤ ከቃሉ ጋር መጽናት አለብን፤ እያችሁ ከድምጹ ጋር።

65 ብዙ ግራ ግብት ያሉ ነገሮች! ሰዎች ተነሰተው፤ ሰለ ቃል እውቀት ሳይኖራቸው፤ ብዙ ይናገራሉ፤ ምናልባትም ምክንያታዊ ሊመስሉ ይችላሉ። ኮሚኒዝምኮ፤ "ሁሉም ሰው አንድ ነው። ካፒታሊሰት የሚባል የለም፤ ሁሉም ኮሚኒሰቶች ናቸው" የሚል ምክንያታዊ ነው፤ ኮሚኒዝም፤ የውሸት ሪቫይቫል ነው ብላችሁ ለማሰብ ቆም ብላችሁ ታውቃላችሁ? ምን መነሻ በማድረግ ነው ይሄን ሁሉ የነደፈው? ... ኢየሱስ፤ "የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ እሰኪያሰት ድረስ፤ ሁለቱ መናፍሰት በጣም የተቀራረቡ ይሆናሉ" ብሏል። የዲያቢሎሰ ነገር ሁሉ፤ እግዚአብሔር የፈጠረውን ማጣመም ነው። ኃጢአት—የጠመመ ጽድቅ ነው። ውሸት የተዛባ እውነት ነው። ምንዝርና—እግዚአብሔር ለእኛ የመደበው ተግባር፤ ተዛብቶ ነው። አለማመን ማለት እምነት ሲጣመም ነው። ጠማማነትን ለመቀበል—እውነቱን መካድ ይኖርባቿል። እያችሁ፤ እነዚህን ድምፆች ግሯቸው፣ በቃሉ ፈትናችሁ እውነት መሆናቸውን ተመልከቱ።

66 ሰለ እነዚህ ድምፆች፤ ብዙ እያልን፤ መቀጠል እንችል ነበር፤ ነገር ግን ጊዜአችን ሄዷል። ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው እሰከማያውቁ ድረሰ ግን፤ በጣም ብዙ ድምጽ አለ። መጨረሻ ሜቶዲሰቱ የባፕቲሰት ሰባኪን ይሰማል፤ እዚያ ይሄዳል፤ በዚያም ትንሽ ይቆይና ወደ ሉተራኖች ይሄዳል። ከዛ በኋላ ወደ ጴንጤ፤ በየዓይነቱ ብዱኖች አሏቸው፤ አንዱ ወደ አንደኛው ይሮጣል፤ ሌላኛውም ወደ ሌላ፤ ከዛም ወዲህና ወዲያ። አለመረጋጋትህ ነው የሚያሳየው። ድምጹን ሰማ! ይኸውላችሁ፤ ድምጹ፤ በወረቀት ላይ ሰፍሯል፤ ድምፁ እውነት ከሆነ ይረጋገጣል።

67 ሁሉም ነገር ትርምሰ ውሰጥ ያለ ይመሰላል። የቤተክርሰትያኑ ዓለም የሚያደርጉት እያውቁም፤ የፖለቲካው ዓለም ትርምሰምሰ ብሏል። ሰዎች ከዚህ ተነሰተው፤ ያልሆነ ነገር ያነሳሉ፤ አንዳንዱ ጃኬት፣ አንዳንዱ ኮት። በሮም በነበርኩ ጊዜ፤ ከኢየሱሰ እጅ ውሰጥ የተለቀሙና የታወቁ አሰራ ዘጠኝ የተለያዩ ሚሰማሮች አሏቸው፤ ግንኮ ሶሰት ብቻ ናቸው፤ አሰራ ዘጠኝ የተለያዩ ሚሰማር አገኘን ይላሉ። አሁን ሚሰማሩን የያዘው ማንም ቢሆን፤ ምን ልዩነት ይፈጥራል? ክርሰቶሰ እምልኩት ብሎ የሰጠን ሚሰማር የለም፤ በቃሉ በኩል፤ የሰጠን መንፈሰ ቅዱሰን ነው! "የሚያምኑ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ ነው ወይሰ የመጀመሪያው ሚሰማሮች ይቀበላሉ"? "የሚያምኑትም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል... ይኖራቸዋል። እኔ የጀመርኳት ተቋም ውሰጥ አባል ይሆናሉ"? ድምፁ እንዴት እንደሚቃረን አዩት? የጀመራት አንድም የለችም።

68 ነገር ግን፤ "የሚያምኑትም **እነዚህ** ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በሰሜ አጋንንትን ያሰወጣሉ።" ቃሉ ይሄው ነው። "በአዲሰ ልሳኖች ይናገራሉ፣ እባቦችን ይይዛሉ፤ አይጎዷቸውም። ገዳይ ነገሮችን ቢጠጡ፤ አይረብሻቸውም። እጃቸውን በታመሙ ላይ ቢጭኑ ይፈወሳሉ።" እነዚህና ሌሎች የቅዱሰ ቃል ክፍሎች ሁሉ አንድ ላይ ሲጣመሩ አሰተውሏቸው።

69 አሁን ይሄ ብቻውን፤ አያረጋግጠውም፤ በጭራሽ። እኛ ጴንጤዎች የተላለፍነው መንገድም ይህ ነው። ኢየሱሰ፤ "በዚያ ቀን ብዙዎች ወደ እኔ ይመጣሉ፤ መጥተውም፤ 'ጌታ ሆይ እኔ በሰምህ ታላላቅ ነገሮች አላደረግሁምን ይሉኛል እላለምን? በሰምህ ትንቢት አልተናገርሁምን? ይህን ሁሉ በሰምህ አላደረግሁምን?'" ኢየሱሰም፤ "እናንተ ዓመጸኞች፤ ከእኔ ራቁ፤ በጭራሽ

አላወቅኋችሁም” ይላቸዋል። እህቶቼ እና ወንድሞቼ፤ ይህን ትውልድ ለምን አብዝቼ እንደምከሰና እንደማወግዝ፤ ገብቷቿል? እንደ ሰዎች እና እንደ መላእክት በልሳን ትናገሩ ይሆናል፤ በቤተክርስትያን ሁሉ በመንፈስ ትጨፍሩ ይሆናል፤ ይህ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

70 መሀመዳውያን እንደዚህ ሲጨፍሩ አይቻለሁ። በጠንቋይ ሐኪሞች ጉባኤ... ከዶክተራቸው ሰምቻለሁ፤ ጠንቋዮቹ ተነስተው በልሳን ሲናገሩ እና ሲተረጉሙት አይቻለሁ፤ ምን ሊሆን እንዳለም በትክክል ይናገራሉ፤ ደግሞም እንዳሉት ይሆናል። እርሳስ እንኳን ተነስቶ በማይታወቁ ልሳኖች ሲጽፍ አይቻለሁ፤ ሊያነበው የሚችልም አንዱ ብቻ ነው፤ እርሱም ከዲያብሎስ ነበር። የዘላለም መድረሻችሁ በተራ ስሜት መሠረት ላይ ማድረግ አይገባም። ሰይጣን እነዚያን ሁሉ ስሜቶች ማስመሰል ይችላል። አይ... በሕይወታችሁ ለውጥ የሚያስመጣ፤ ክርስቶስን ማወቅ ነው። ሕይወታችሁን ፈትሹት እና ከቃሉ ንድፍ ጋር መዝኑት፤ ከዛ በኋላ የት እንዳላችሁ ተመልከቱ። በትክክል፤ ቆጠራ አድርጉ።

71 በዚህ ሁሉ አስመሳይነት፣ ሐሰተኛ ድምጾች፣ ሐሰተኛ ነብያት፣ ሌሎች ገና እየተነሱ ያሉ ነገሮች ሁሉ፤ በዚህ ሁሉ ግን፤ አሁንም ኢየሱስ፤ “ማንም ድምጼን ሰምቶ ቢከተለኝ” ይላል። ቃል ነው። በነዚህ ድምጾች ሁሉ፤ ዛሬ ለእኛ ያለውን ትዕዛዝ፤ አድምጡ። ድምጹም፤ ሌሎች ድምጾች ሁሉ ለማውጣት ብዙ ጊዜ ይፈጃል ያልኩት ነው። የሚያሳዝን ነገር ነው፤ ህዝቡን እጅግ ያወዛግባል። አሁኑኑ ተቀበሉት፤ ደግማችሁ፤ ሁለተኛ፤ ዕድል አታገኙም። ዛሬ ዕድሉ ሊያመልጣችሁ ይችላል። ምናልባትም ነገ ዕድል አታገኙም ይሆናል። አሁን ነው! “ድምጼን ሰትሰሙ፤ በማስቆጣት ዘመን እንደነበረው፤ ልባችሁን እልኸኛ አታድርጉት። ጊዜው አሁን ነው። ድምጼን የሚሰማ ማንም ቢኖር የተወደደች ጊዜ ይህች ናት።” ይህም በትርምሶች ሁሉ መካከል እንኳን ድምጹ አሁንም ህያው መሆኑን ያስረዳል። አሁንም ድምጽ አለው! ለምን? ድምጹ ለዘላለም ጸንቶ ስለሚኖር። ይሄውላችሁ፤ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ድምጼ ግን አያልፍም” ቃሉን።

72 እስኪ ሌላ፤ አምስት ደቂቃ ብቻ፤ በፍጥነት፤ እንውሰድ። ያን ያክል ትታገሱኛላችሁ፤ ወይም ትንሽ ደቂቃ፤ ትሰጡኛላችሁ? ፈጠን፤ ፈጠን እላለሁ። እስኪ ይህን ድምጽ ሰምተው የታዘዙትን ጥቂቶች እንመልከት። እንዴት አስቻላቸው፤ ማንስ የገፋፋቸው። አሁን፤ ብዙ—ቅዱስ ቃላት እያለፍኩ እሔዳለሁ፤ ሕይወታቸውን እና ያላቸውን ነገሮች ሁሉ እንዴት እንደለወጠ፤ በትክክል እንዲገባችሁ: እንዴት ወጣ ሞኞች ሆኑ፤ “ቂል” ብለን እንጠራቸዋለን። እግዚአብሔርን ያመነ ሰው ሁሉ፤ እንደ ቂል ይቆጠር ነበርና። ምክንያቱም፤ እንደ ዓለም አካሄድ ከሄዳችሁ፤ የሆነ ችግር ቢኖርባችሁ ነው። ክርስቲያን ለመሆን ሞኝ መሆን አለባችሁ። “በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ የሚኖሩ ሁሉ በዓለም ላይ ይሰደዳሉ። በዓለም ነበረ፣ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፤ ዓለሙም አላወቀውም።” በፍጥነት አሁን፤ በማጠቃለያችን በደንብ ስሙኝ።

73 አዳም ሲመሽ ድምጹን ይሰማል፡ ከእሱ ጋርም፡ ህብረት ያደርጋል። አዳም ኩነኔ አልነበረበትም። የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ፤ “አባ፤ አሁን ልረፍ፤” ይላል። እሱ ሲተኛም፤ ሄዋንም በክንዱ፤ አንበሳው፣ ነብር፣ እና የበረሃ አራዊት፤ በዙርያው ይተኛሉ፤ መጎዳዳት አልነበረም፤ መታመም አልነበረም፤ በማለዳ

ተነሰቶ ይነቃሉ እንጂ፤ መቅበዝበዝ አልነበረም። አዳም መሰማት በሚገባ መልኩ ድምጹን ሰምቷል።

74 አንድ ቀን ግን የሚሰቱን ድምፅ ሰማ። ለተወሰነ ጊዜ ይሄኛውን ብተወው ይሻላል። የተሳሳተውን ድምጽ ሰማ፤ ግን እኮ፤ በምድር ካለ ነገር ሁሉ የሚቀርበው፤ የሚሰቱ ነው። ለምን እንደ እዮብ፤ “አንቺ እንደ ሰነፍ ሴት ተናገርሽ” አላላትም? እንዲህ ቢያደርግ ኖሮማ፤ መላ የሰው ዘር ከመሞት ይልቅ መሰንበት ይሆንለት ነበር። የሰው ልጆች እና የጊዜን ሰርዓት ሁሉ ቀያየረው። የእግዚአብሔር ድምጽ ግን ሰምቷል፤ ከድምጹም ጋር ሕብረት ያደረገ፤ ሲክደው ግን... ሚሰቱ ጥፋተኛ እንደነበረች እንዴት አወቀ? አሰቡት፤ ይገርማል።

75 ዛሬ ዛሬ ድርጅቶቻችን፤ እና ቸርቾቻችንን፤ እግዚአብሔር በብልጽግናችን ፈገግ የሚል ይመስለናል። ሚኪያሰ በአራት መቶዎቹ ነብያት ፊት በቆመ ጊዜ ነገሩ ውብ ይመሰል ነበር። መልካም ይመሰላል፤ ምድሪቱ የእነሱ ሆና፤ ፍልሰጤማውያን፤ ወይም፤ ሶርያውያን፤ በውሰጧ እየኖሩ፤ ጥሩ ነገር ይመሰላል። ነብያቱም “ሂድ ተከናወን፤ ምድሪቱ የእኛ ናት። ውሰዳት አሉ!” ግን እኮ የእግዚአብሔር ድምጽ አይደለም። ሚኪያሰም ዞር አለና ድምጹን ገሰጸው። እንዴት አውቆ ነው እንዲህ ያረገው? ምክንያቱማ ራእዮ ከቃሉ ጋር አንድ ሰለነበረ ነው። ዛሬም ታይቶ ለመታመን ብቸኛው መንገድ ይሄው ነው፤ ከቃሉ ጋር መሰማማት አለበት።

76 ከዛሰ በኋላ አሰተውላችኋል? አዳም ከእግዚኣብሔር ቃል ይልቅ ሌላ ድምጽ፤ የሚሰቱ ከሰማ በኋላ... ቤተክርሰቲያንም ከቃሉ ይልቅ ከራሷ የሃይማኖት ትውፊቶች ጋር ተዳቅላ፤ የድርጅቷን ድምጽ ትሰማለች፤ መኖር ባማራቸው መንገድ እንዲኖሩ ይፈቅድላቸዋለች። ብቻ ቤተክርሰቲያን ይሂዱ የቤተክርሰቲያን አባል እሰከሆኑ ድረሰ፤ ዋናው ነገር ይህ ነው። እማኝ የምድር የቅርብ ዘመዱ፤ እንደነሱ አባባል፤ ቤተክርሰትያን ናት። ለአማኝ፤ ለእውነተኛው አማኝ ግን፤ የቅርብ ዘመዱ መንፈሰ ቅዱሰ ነው፤ የእግዚአብሄር ቃል ነው።

77 ከዛ በኋላ አዳም ሁኔታውን ሲያሰተውል ታያላችሁ፤ የእግዚኣብሄር ድምጽ ዳግም ሲጠራው ሰማ፤ ያኔ በበለሰ ቅጠል ውሰጥ ገብቷል፤ “ይህን ለምን አደረግክ? ” የሚለው የኩነኔ ድምጽ ነበር።

78 ዛሬ እደነቃለሁ፤ አሜሪካ ወይም ዓለም በዚህ የሃይማኖታዊ ጫጫታ፤ ባለበት ሁኔታ፤ አሜሪካም እየዋጠች፤ ተውጣለች፤ በቅርብም ብሔራዊ ሃይማኖት ይሆናል። [ባዶ ቦታ በቴፕ ላይ—እርታዒ።]

79 አውቃለሁ እነዚህ ቅጂዎች ናቸው በምድርም ሁሉ ላይ እንደሚሄድ አውቃለሁ። የሚያበጅልኝ ማን አለ? እያንዳንዷ መልዕክት መላውን ዓለም፤ ሌሎች አገራት ሁሉ የሚያካልል፤ የቴፕ ፕሮግራሞችም አሉን።

80 ካሰተውላችሁና ካያችሁ፤ ግን፤ በበለሰ ቅጠል ቆማችኋል። እውነተኛው የእግዚአብሔር ድምፅ ሲመጣ፤ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። ግራ ያጋባቸዋል፤ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም።

81 ቶሎ ብለን፤ ኖህ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰማ። ህይወቱን ለማዳን ይዘጋጅ ነበር፤ መመርያዎቹን ሁሉ ተከትሎ ጸና።

82 አሁን ስሙኝ፤ አትድከሙብኝ፤ ሰው ድምጹን ከሰማ… ይሄን በደንብ ያዙ። አንድ ሰው የሆነ ድምጽ ሰምቶ፤ የሰማውም ድምጽ የእግዚአብሔር መሆኑን ከተረጋገጠ፣ ወቅታዊ ከሆነ፣ ከዚያ በኋላ በሰውየው እንደበት ከተነገረ፣ ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንጂ ቃሉ አያልፍም።

83 ኖህ ድምጹን ሰማ፤ ዓለምንም ኮነነ። መልእክቱ—እነርሱ ከደረሱበት ሳይንሳዊ ልቀት ጋር ስላልተጣጣመ፤ በፊቱ ሰቀውበታል። ይሁን እንጂ ዝናብ ዘንቦ ዓለምንም አጥፍቷል። አያችሁ? በተነገረው ድምጽ ውስጥ፤ ዘሩ በዚያ ውስጥ ነበረ። በእያንዳንዱ ዘመንም ያው ነበር።

84 ሳሙኤል፤ የእግዚአብሔር ድምጽ በሰማ ጊዜ፤ ዔሊን ለመገሰጽ… መሄድ ስለነበረበት ደንግጦ፤ እንክብካቤ ያደረገለትን ሰው። ደግሞም አብልቶ ያሳደገውና አባት የሆነለትን ሰው ነው።

85 አገልጋይ ወንድሞች ሆይ፤ ልናገር? ብዙ ጊዜ፤ አገልጋዮች፤ በሀይማኖት ተቋሞቻችሁ መሠረቶች እና አቋሞች፤ የብቃት ማረጋገጫ በኪሳችሁ፤ ያሳደጓችሁ ድርጅት፤ የመገባችሁ እና እንክብካቤ ያደረገላችሁ ቡችሎች የሆናችሁ በቤተክርስትያን ሀላፊነት ተሰጥቶአችሁ፣ በጉባኤም ውስጥ ያስቀመጧችሁ፤ ለትምህርታቸው መታሰር ግድ ነው። አያችሁ? ለእውነተኛ የእግዚአብሔር ባርያ እጅግ ይከብዳል የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ ወደ ዋናዋ እናት ድርጅት መመለስ፤ “ይሄ ቃል ስላልተቀበላችሁ ተኮንናኋል።” ይበል፤ ይከብዳል!

ለሳሙኤል ከባድ ነበር። ነቢይ ስለነበረ ግን፤ ማድረጉ ግድ ሆነ። ምንም ቢጎዳ ወይም ባይጎዳ፤ ለማንኛውም ማድረግ ነበረበት።

86 ሙሴ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቷል። በስነመለኮት የተጠቀጠቀ ነበር። **መግቢያ** እና **መውጫውን** ሁሉ ያውቃል፤ ነገር ግን ወደቀ። የእግዚአብሔርን ድምፅ ከሰማ በኋላ፤ ሙሴ በጭራሽ እንደ ድሮው ሆኖ አልቀረም።

87 ማንም ቢሆን እንዲሁ አይቀርም። ሲናገር—ድምጹን በጆሮአችሁ ልትሰሙት ትችላላችሁ፤ የሚናገረው ድምጽ፤ በልባችሁ ስትሰሙት ግን፤ አያችሁ፤ መሰማት ጀምራቿል። በዓይኖቻችሁኮ አታዩም። በዓይናችሁ ትመለከታላችሁ፤ በልባችሁ ታያላችሁ። አንድን ነገር ተመልክታችሁ “አልታየኝም፤” ስትሉ፤ አልገባኝም ማለታችሁ ነው። የምትሰሙት በጆሮአችሁ አይደለም፤ የምትሰሙት በልባችሁ ነው። ብዙ ጊዜ ጆሮዋቻችሁ ትክክል የእግዚአብሔር ድምፅ ይሰማሉ፤ በኋላ ግን ከዳክዬ ጀርባ እንደሚራገፍ ውሃ ከእናንተም ይተናል። በእውነት ግን ስትሰሙ፤ በልባችሁ ትሰማላችሁ።

88 ሙሴ ያንን ሁሉ ቲኦሎጂ ይዞ፤ የእግዚአብሔርን ድምጽ አልሰማም። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር ይህንን የሰማንያ ዓመት የበግ እረኛ ወደ አንድ ጠርዝ ጠርቶ አነጋገረው፤ ያዘውም። አምላክነቱም አረጋገጠ። በሙሴ ላይ ያደረገው የመጀመሪያ ነገር፤ ቃሉን መግለጥ ነው፣ “የገባሁትን ቃል አስቤአለሁና፤ እወርዳለሁ።”

89 ለዘመን ፍጻሜ የገባው ቃልም ይህ ነው። ከአሕዛብ ዘንድ አንድን ህዝብ ያስነሳል፤ ሌሎች ቃል የተገቡ ተስፋዎችም ጭምር።

90 “ይህን ቃል ገብቻለሁ።” “ሙሴ ጫማህን አውልቅ” አለው። በሌላ አገላለጽ፤ አክብረው። “አሁን በትርህን ጣል።” እና—ያቺ ደረቅ የበረሃው ብትር እባብ ሆነች፤ ሙሴ ሲይዛት፤ ወደ ቀድሞ ተመለሰች። አያችሁ? እግዚአብሔር መሆኑን አውቋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር፣ ሲናገረው የነበረው ቃል፣ እንዲህ ብሎታል፤ “በእጅህ የያዝከውን ብትር ጣለው።” የእግዚአብሔር ቃል ነው። ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ አትሞክሩ፤ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ለሙሴ እንጂ፤ ለእናንተ አይደለም። **ይሄው** የእናንተ የእግዚአብሄር ቃል! “ብትሩን ወረወራት።” ወደ እባብ ተቀየረች። አለውም፤ “አሁን ፈረተኸዋል? በል በጭራው አንሳው፤” ውደ ቀድሞው ተመለሰ። የመጣለት የእግዚአብሔር ቃል። ምን አደረገለት? እግዚአብሔር ቃሉን አረጋገጠለት።

91 ከጥቂት ወራት በፊት ተደውሎልኝ፤ ስለ፤ ከ፤ ኦህ ፤ ከአንድ ዓመት ገደማ፤ ከአንድ ዓመት በፊት። አንዲት ሴት ከባፕቲስት ሰባኪ እና ከጴንጤቆስጤ ሰባኪ ጋር፤ በስልክ መስመር ውስጥ። “ወንድም ብራንሃም፤ ጌታ እኔን ነብዩት አድርጎኛል።” አለችኝ፤

“ጥሩ።” አልኳት።

92 “ታውቃለህ፤ አገልግሎቴ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ—መናገርህን ተነግሮኛል።” አለች።

93 አሁን እኔ፤ ይሄን ላደርግ አላደርግም፤ ከቃሉ ጋር አይስማማም። ስለዚህ አልኳት፤ “እመቤት፤ ይህ ስህተት ነው። እንደውም አላውቅሽም።”

94 የባፕቲስቱ ሰባኪም፤ ሲናገር ሰማሁት፤ የጴንጤቆስጤ ሰባኪውን ሰማሁት። “እና፤ እዚህ ጉባኤ እያደረግኩ ነው።” አለች። አክላም አለች፤ “ጌታ ድንቅ ነገሮች እያደረገ ነው።”

95 እኔም “በዚህ ነገር እኔም ደስተኛ ነኝ።” አልኳት። እኔም “እስካሁን አንዳች ነገር ነግሮሽ ያውቃል? ” አልኳት፤ እሷም አለች…

“አዎ፤ ያዘጋጀሁት ታላቅ ብሮግራም አለ።” አለች።

96 “በጣም ጥሩ።” አሁን፤ “ፕሮግራምሽ ምንድነው? ” አልኳት። “ጌታ ምን ነገረሽ? ” አልኳት።

97 “እሱ ያለኝ፤ ‘በዚህና በዚህ ቀን፤ ወደ ፊኒክስ፣ አሪዞና፣ ሄጂና፤ የተሰወረውን የዳችማን የወርቅ ማዕድን ሰፍራ እሰጥሻለሁ፤ አንቺም በዚያ ቦታ የሚገኝ ወርቅ ትወስጂአለሽ በዓለም ዙርያ የሚገኙ ሚሽነሪዎችን ስፖንሰር ታደርጊያለሽ።’” የጠፋውን የደችማን ወርቅ ማዕድን ሰፍራ አፈታሪክ መሆኑን ሁላችን እናውቃለን። “ስለዚህ ብሏል።”

98 “መልካም፤ እግዚአብሔር መሆኑን አለመሆኑን እንዴት እንድምታረጋግጭ እነግርሻለሁ።” አልኳት። በይ አልኳት፦ “በዚያ ቀን በሰፍራው ተገኚና። የጠፋውን የዳችማን ማዕድን ካገኘሺው፤ እንግዲያውስ እግዚአብሔር ነው። የጠፋውን የዳችማን ማዕድን ካላገኘሺው፤ ንሰሓ ግቢ ያንን የሐሰት መንፈስ ከአንቺ አርቂ።” እግዚአብሔር መሆኑን አለመሆኑን ለማወቅ እንዲህ ነው።

99 እግዚአብሔር፤ "ሙሴ፤ ብትርህን ወርውረው፤ ወደ እባብ ይቀየራል" አለው። እሱም አደረገው። "እንደገናም አንሳውና ብትር ይሆናል።" አለው፤ አደረገው።

100 እግዚአብሔር በዘመኑ ፍጻሜ ለሚኖር አገልግሎት ቃል ሲገባ፤ እሱ አደርጋለሁ ብሎ እንደተናገረ እንዲሁ ያረጋግጣል። ከዛ በኋላ ትክክለኛ ድምፅ እንዳገኛችሁ፤ ትክክለኛ ነገር መሰማታችሁን ታውቃላችሁ። የተረጋገጠው ቃሉ ስለሆነ። አያችሁ? አው፤ እንዴት... አዝናለሁ፤ እኔ... ይሁን።

101 ሙሴ እንግዳ ነገር ፈጸመ። ሙሴ—ምን ዓይነት አሰቂኝ ስራ እንደሰራ ተመልከቱ። ሁሉጊዜ፤ የእግዚአብሔርን ድምፅ ስትከተሉ፤ ለዓለም፣ እብዶች ናችሁ። በሚቀጥለው ቀን፤ ሙሴ ከሚስቱ ጋር፤ በቅሎ ላይ ወጥተው፤ ታናሹን በወገቧ፤ ደቡባዊው፤ "ልጅ" በወገቧ ላይ አድርጋ፤ ወጡ። ሽማግሌው ጺሙን **እንደዚህ** ተንጠልጥሎ፤ ራስ በረሃው እያበራ፤ ዱላ በእጁ ይዟል፤ ትንሹን አህያ እየመራ፤ መሄድ የቻለውን ያህል ወደ ግብጽ አመራ። አንድ ሰው "ሙሴ፤ ወዴት ትሄዳለህ? " ሲለው፤

102 "ድል ለመንሳት፤ ወደ ግብጽ እየወረድኩ።" ወጣት ሆኖ ያልቻለውን፣ ጦረኛ ሆኖ ያልቻለውን፣ አሁን ግን ድል ለመንሳት እየወረደ ነው። አደረገውም። ለምን? የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቷል በዘመኑ ሲገለጥም ተመልክቷል፤ በዘመኑ ሊሆኑ የተገባቸው ነገሮች፤ ሲሆኑ አይቷልና

103 ራሱ-ገዝ የነበረ ፈሪሳዊ፤ ጳውሎስ፤ የቻለውን ቲኦሎጂ ሁሉ የሞላ ሰው፤ አንድ ቀን የእግዚአብሔር ድምጽ ሰማ። የእሳቱን ዓምድ አየ፤ እና የተለየ ነገር እንዳለ ተገነዘበ። ሕይወቱን ለውጦታልና። ምንም ያህል ፈሪሳውያን ፣ ሰንት ገማልኤላውያን ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር ጳውሎስን "ተሳስተሃል፣ ተሳስተሃል" ብሎ ቢጮኽም፤ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቷል፤ እውነት መሆኑንም አውቋል።

104 ጴጥሮስ፤ ሐይማኖተኛ ሆኖ፤ የአባቶች ወግ የሚጠብቅ፣ ያገኘውን ስጋ ሁሉ የማይበላ ነበር። በጭራሽ፤ አያደርገውም። በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳች ማድረግ አይቻለውም። ቃል በቃል፤ የሽማግሌዎችን ወግ ያለነቀፋ ይጠብቅ ነበር። ምን ገጠመው? አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማ። "የቀደስኩትን ነገር፤ ርኩስ እና የሚያስጸይፍ አትበል።" ጌታ ወደላከው የትኛውም ቦታ ለመሄድ የተዘጋጀ። የተለወጠ ሰው ነበር።

105 በመዝጊያ ላይ ፣ ይህን ልበል። አንድ ጊዜ አንድ አማኝ ሰው ነበር። ለአራት ቀናት በሞት የቆየ ሰው። እየሸተተ፤ በመቃብር ውስጥ ቆይቷል፤ በሰብሶ ነበር፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ድምፅ "አልዓዛር ሆይ፤ና ተነሳ!" ሲለው ሰማ። ሰውን ከሞት እና ከመበስበስ ከመለሰ፤ በውስጧ ሕይወት ላላት ቤተክርስቲያንስ ምን ያደርግ ይሆን? ከተነጋገርንባቸው ድምፆች ውጥንቅጥ ውስጥ፤ እነሱን ማንሳት አለበት፤ ከሐይማኖት፣ ከፖለቲካ፣ ከሆሊውድ፣ ከየሐሰት ትቢቶች እና ከሌላ ነገሮች ሁሉ። በዚህ ሁሉ፤ እውነተኛ የእግዚአብሔር ድምፅ፤ በኃጢአት፤ እና በደል፤ የሞተውን ሰው፤ እንደገና ወደ ሕይወት ይጠራዋል። የወደቀች ቤተክርስቲያንን እንደገና ወደ ሕይወት ይጠራት ዘንድ ይገባል። በእርግጥ!

106 አስታውሱ፤ በመጨረሻ፤ ይህንን ልበልና፤ እዘጋለሁ። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “በመቃብር ውስጥ ያሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ድምፅ የሚሰሙባት ቀን ትመጣለች” እናንተም ትሰሙታላችሁ። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑም፤ መስማታችሁ የማይቀር ነው። ከመቃብር ከሚወጡት፤ አንዳንዶች ለኩነኔ ይመጣሉ። ድምጹን ይሰሙታል፤ ነገር ግን የሚኮንናቸው ድምጽ ነው። እናም ዛሬ ብትሰሙ፤ “ከስንት ጊዜ በኋላ፤ ዛሬ፤ ድምጹን ብትሰሙ፤ ልባችሁን እልኸኛ አታድርጉ፤ በማስቆጣት ዘመን እንዳደረጋችሁት።” እናንተ፤ ጴንጤዎች በሕግጋት፤ እና በአለማዊነት፤ እራሳችሁን የምትመዳድቡ፤ “የአምልኮት መልክ ይዛችሁ ኃይሉን ግን የምትክዱ፤” ለኩነኔ መነሳት ሳይሆንባችሁ፤ ምክንያቱ አሁን በቃሉ የሚያጠነቅቃችሁ የእግዚአብሔር ድምፅ በዚያ ቀን ግን ያወግዛችኋል።

107 ለብ ያላችሁ አማኞች ከሆናችሁ፤ የእግዚአብሔር ድምፅ ዛሬ ጠዋት በልባችሁ ውስጥ ይጮኻል፣ “የለብታ አማኝ፤” ንስሐ ብትገባ ይበጅሃል!

108 እናንተ ለክርስቶስ የማትኖሩ፤ ጎልማሶች፣ እመቤቶች፣ ወንዶች እና ሴቶች፤ የእግዚአብሔር ድምፅ በቃሉ “ይህን ማድረግ አቁሙ፤” በማለት ያስጠነቅቃችኋልና፤ ብታቆሙ ይሻላል። ምክንያቱም አንድ ቀን እንደገና ትሰሙታላችሁ፤ ያኔ ያወግዛችኋል። አሁን እየተናገራችሁ ነው፡ ልትክዱት አይቻላችሁም። እና፡ መቀዳቱን፡ አትርሱ።

109 ድምፁን ሰምተው ቅን ነገርን የሚያደርጉ፤ ወደ ጽድቅ፡ ወደ ክብርና፡ ወደ ሰማይ ከፍ ይላሉ።

110 ስለዚህ አንድ ቀን የእግዚአብሔርን ድምፅ ትሰማላችሁ። ምናልባት ዛሬ ጠዋት ደካማ በሆነ ሁኔታ ለልባችሁ ተናግሮ ይሆናል፤ ከሄድክበት መንገድ፤ እንድትመለስ፤ ወደ እግዚአብሔር እንድትዞር። አስታውሱ፤ ለልባችሁ የተነገርውን ድምፅ፤ አሁን፤ በገነት እየተቀዳ ነው። አንድ ቀን ኢየሱስ ሲጠራ፤ በመቃብር ውስጥ ያለው ሁሉ፤ ጻዲቁም፣ ሐጥያተኛውም፤ ሁሉ ይነሳል። ከዚያ በኋላ ያኔ ይህ እራሱ ድምጽ ወደ እናንተ መጥቶ ያንሾካሹክባቿል “በፊኒክስ፣ አሪዞና፣ በእሁድ ማለዳ፤ ስለ ድምጹ እየነገረ፤ አገልጋዩ ብዙ ሰዓት ባቆያችሁ ጊዜ፤ እኔ ነገርኳችሁ፡ ሴቶች ጸጉራችሁን እንድታሳድጉ፤ ሥነ ምግባር የጎደለው አለባበስ እንድታቆሙ ነግሬአችኋለሁ: ወንዶች መዋሸትን፣ ማጨስን፣ አቁሙ ብያለሁ: ለእናንተም ለሰባኪዎች ወደ እግዚአብሔር ቃል ተመለሱ ብያለሁ።” ምን ማለቴ እንደሆነ ተመልከቱ? ትክክል ነው።

ያቺ ጸጥ ያለች ድምጽም፤ “ትክክል ሊሆን ይችላል” ትላለች።

111 እንደ ኒቆዲሞስ መምጣት ካለብኝ፤ አሁንም እዚያው ለመድረስ እሞክራለሁ። ወደ በረሃው ወደ አንዲት ቦታ እወጣና፣ ወደ እርሱ መጥቼ፤ እንዲህ እለዋለሁ፤ “ጌታ እግዚአብሔር፤ እነሆኝ አሁን ቀይረኝ። እንደ እስራርህ ቅረፀኝ።” ተመለሱ ወደ ቃል። ከቃል ፈቀቅ ብላችሁ እራሳችሁን ካያችሁበት ስፍራ፤ ወድያውኑ ወደ ቃሉ ተመለሱ፤ ምክንያቱ የስንስለት ብርታት በደካማው ጎኑ ነው። እናም ባሕላችሁን ለማራመድ ብላችሁ፤ የእግዚአብሔር ትዕዛዛትን በተላለፋችሁበት የትኛውም ስፍራ ላይ፤ በሌሎች ነገሮች ላይ ምንም ያህል የጸናችሁ ብትሆኑም እንኳ ስንስለታችሁ የሚበጣጠስበት ስፍራ በዛው ላይ ነው። የማትለዋወጠው የእግዚአብሄርን እጅ ያዙ።

112 እንጸልይ። ዛሬ፤ ጌታ ሆይ፤ ከብዙ ጊዜ በኋላ፤ እንደምትናገር ነግረሃል፤ ሕጎችህ በልብ ጽላቶች ላይ እንደምትጽፍ። ከፊቴ ምን እንዳለ አላውቅም። እኔ የማውቀው ቃልህን ተቀብየ ማሰራጨት ብቻ ነው፤ በርግጥ ደግሞ በሆነ ቦታ በአንዳንድ አለቶች ሰር ላይ ያርፋል። አምላክ ሆይ፤ ለእያንዳንዱ ወጣት፣ ለጎልማሳው፣ ለአዛውንቱ ሁሉ፣ ምንም ይሁን ምን፡ እንድትናገራቸው እጸልያለሁ። ለእኔም ጌታየ፤ ለልቤ ተናገር። በአገልጋዮች ልብ ተናገር። በጉባኤው ልብ ተናገር።

113 ኣባ፤ ዛሬ ድምጽህን እንሰማው ዘንድ፤ እንጸልያለን። ደግሞም በሳሙኤል ዘመን፤ የተገለጠ ራዕይ ጥቂት እንደነበረና፣ ህዝቡንም እንዳዛለ፤ እናውቃለን። ዛሬም ያው ነው። ህልም እና አላሚዎች አሉን፣ ተናጋሪ እና ተርጓሚዎች አሉልን፤ ነገር ግን ከእግዚአብሄር ቃል ጋር የሚመጣና የሚያርም... የተገለጠ ራዕይ፤ የሰማይ አባት ሆይ፤ በምድረበዳ ላይ፤ “የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤” ብሎ የሚጮኽ ድምጽ፤ “ለጌታ መምጣት ተዘጋጁ!” ዛሬም ያንን ድምጽ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ እናምን ዘንድ እንጸልያለን፤ እንዴት ያለ ሞኝነት ነው፤ ድምጹን ለማሰወገድ እና ለማፍዘዝ ብዙ ድምጽ እያለ፤ በሚሰማው ጀሮ ዘንድ ግን ርህሩህ ነው። መንፈስ ቅዱስ አሁን በሁላችንም ልብ ውስጥ ሥራውን እንዲሰራ እፀልያለሁ።

114 ራሶቻችን ዝቅ እንዳለ፤ ልባችንም ዝቅ ማለቱ አምናለሁ: በሕይወታችሁ ውስጥ ያልታዘዛችሁለት ነገር ካለ፤ ቅዱስ ቃል አውቃችሁ፤ የመጽሃፍ ቅዱስ አስተምህሮት የማይፈቅደው መሆኑ የምታውቁ፣ ምክንያቱ ደግሞ የሆሊውድ ድምጽ፤ ክፉ እንድትፈጽሙ ሰላደረጋችሁ ብቻ። እናንተም አገልጋዮች የሆናችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ፤ እውነትቱን ተረድታችሁ፤ ፍጹም እውነት መሆኑን አውቃችሁ፤ ይሄን ካስተማራችሁ ግን ከድርጅት እንደምትባረሩ ታውቃላችሁ። እናንተም የስሕተት ነገር የተከተላክችሁ፤ ይህን የጥፋት ህይወት ተውት። እናንተ ልጆቻችሁን የማትቀጡ አባት እና እናቶች፤ ለማሳደግ የማትሞክሩ። የተቻላችሁን ሞክሩ፤ በዘፈቀደ ዓለማዊ አካሄድ እየሄዱ ናቸው፤ እናንተም ግን በፊታቸው ምሳሌን ታሰቀምጣላችሁ። ይህን እየተገበራችሁ ካልሆናችሁ፤ የእግዚአብሄር ድምጽ፤ “ይህን አታድርጉ” ይላችኋል።

115 አሁንም ዓይኖች ሁሉ እንደተጨፈኑ ራሶችም ሁሉ እንዳቀረቀሩ፤ የሰማይ አምላክ የተራበውን የሰው ልብ ውስጥ ይመለከት የቱ ጋር እንደሳቱም ፈልጎ ይወቅላቸው። እጆች ወደ እግዚአብሔር እንደተነሱ፤ “ጌታ ሆይ፤ ድምጽህ አለማመን ሁሉ እንዲወገድልኝ በእውነት እመኛለሁ፤ እያላችሁ፤ የአንተ ያልሆኑ ነገሮች ሁሉ፤ መሆን የምትፈልገኝ እንድሆን አድርገኝ።” እጆቻችሁን ከፍ አድርጋችሁ፤ በማድረጋችሁ... ? ጌታ ይባርካችሁ። እግዚአብሄር ይባርካችሁ።

116 መጽሐፍ ቅዱስም ተናግሯል፣ እነኚህ ድምፆች ሁሉ እያሉ፤ ኢየሱስ ሲናገር “ማንም ድምጼን ቢሰማ” አለ። እሱን ተከተሉት፣ መሻታችሁን ታገኛላችሁ።

117 ጌታ ሆይ፤ ጊዜው አልቋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሲናገር፤ “ያመኑ ሁሉ፤ተጠመቁ” ይላል። የሰማይ ኣባት ሆይ፤ በእውነተኛ ንስሐ፤ እያንዳንዳቸው እነዚህ እጆቻቸውን ያነሱ ሁሉ፤ ባነበቡት የእግዚአብሔር ቃል፤ ተሳስተው እንደነበሩ የተረዱ ሁሉ። መጠበቅ የአንተው ነውና። ጌታ ሆይ፤ ግማሽ ያህሉ እንኳን ፍጹም አልጠበቅኩም፤ ጥበቃ የእኔ አይደለምና። በተነሱት

እጆች ጀርባ ያለውን ሐሳብ እና ዓላማ አንተ ታውቃለህና። ከዚህች ሰዓት ጀምሮ፤ በልባቸው፤ እንዲህ ያቅዱ፦ “ከዚህች ቀን፤ በኋላ፤ ምንም ዋጋ ቢያስከፍለኝም፤ የእግዚአብሕሄር ቃል እና የእግዚአብሄር ድምጽ እከተላለሁ ይበሉ።” ሲሄዱም፤ በልባቸውም ውስጥ፤ የዚህን ግጥም ዝማሬ ይያዙ፦ “ኢየሱስ መስቀሉን ብቻውን ተሸክሞ፤ ዓለም ሁሉ በነጻ ይሂድ ወይ? የለም፤ ሁሉም ሰው መስቀል አለው; ለእኔም መስቀል አለኝ። ሞት ነጻ እስኪለቀኝ ድረስ፤ ይህን ቅዱስ መስቀል እታገሳለሁ።” የእግዚአብሔር ድምፅ በተሰማ ጊዜም፤ “የቃሉን ድምጽ፤ ድምጹን ተከትያለሁና፤ በጽድቁ እወጣለሁ።” ጌታ ሆይ፤ አሁን ለአንተ አደራ ሰጠኋቸው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

118 አሁን አንገታችንን እንደደፋን፤ ኃጢአችሁን እና ቃልኪዳናችሁን ታደርጋላልችሁ። ጭንቅላቱን ጠምዝዞ፤ በተቀመጠው ያ ህጻን ልጅ ተገርሜአለሁ። ለቤተክርስቲያንም፦ “እኔ ደዌሽን ሁሉ የምፈውስ ጌታ ነኝ” የሚል ድምጽ አላት። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ ድምጽ ነው። እና ፈውስ የምትፈልጉ ሁሉ፤ ቅን ነገር ምን እንደሆነ የምታውቁ እና እያንዳንዱ የእግዚአብሄርን ቃል በቅድስና የምትኖሩ ሆናችሁ፤ ፈውስ የምትፈልጉ፤ እጆቻችሁን እንድታነሱ እጠብቃለሁ። እጆቻችሁ እያነሳችሁ፤ “ጌታ ሆይ፤ ፈውስን እሻለሁ።” መልካም።

119 አሁን፤ “ደዌሽን ሁሉ የምፈውስ ጌታ ነኝ።” የሚል ድምጽ በልባችሁ እየያዛችሁ፤ ቃል ከተነገረ፤ መፈጸም እንዳለበት፤ አስታውሱ። ኢየሱስ፤ በማርቆስ 11:22፦ “በልባችሁ ሳትጠራጠሩ ይህን ተራራ ‘ተነቀል’ ብትሉት፡ የተናገራችሁት እንደሚፈጸም ግን አምናችሁ ብትሉት፤ የጠየቃችሁት ሁሉ ታገኛላችሁ።”

120 አሁን፤ እያንዳንዳችን በየራሳችን እንሁን፤ አሁኑኑ አንገታችን ዝቅ አድርገን፤ የየራሳችሁ ቃል እናውጣ፤ “ጌታ ሆይ፤ ቃልህን አምናለሁ። ትናንት ፣ ዛሬ እና ለዘለአለም ያው እንደሆንክ ስትናገር ድምፅህን ሰምቻለሁ።” እጆቼን በዚህ ልጅ ለመጫን እወርዳለሁ፤ ይህ ሁሉ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት ገና ነውና፤ በልጄ ዮሴፍ ዕድሜ እና መጠን የሚገኝ፤ ውብ ህጻን ልጅ። ሁላችሁ፣ “ጌታየ፤ ድምጽህን ሰምቻለሁ፤ እኔ አምናለሁ።” እያላችሁ እንድትጸልዩ እፈልጋለሁ።

121 የሰማይ አባት ሆይ፤ ስለ ስጋቸው ፈውስ ጉባኤውን ሁሉ በፊትህ እናቀርባለን። እንዲሁም፤ ጌታየ፤ ይህ ጨቅላ እዚህ ተቀምጦ እስከ መልዕክቱ ፍጻሜ ድረስ ቀልቤን ሰቦኛል፤ ቤተሰብ ይህን ህጻን ልጅ ደግፎ ተቀምጠው እያየሁ። በሕክምና ሳይንስ ለዚህ ጨቅላ ተስፋ የለም። በሁሉም ነገር ላይ የሚዘል የእግዚአብሔር ድምፅ ግን አለ። እንዴት እንደሚደረግ የማውቀውን ትዕዛዛትህን ለመፈጸም ይቺ ቤተክርስትያን አንድ ሆናለች፤ አባ፤ ቀሪው ግን የአንተ ነው። እጆቼን በዚህ ጨቅላ ላይ ለማኖር ወደታች እወርዳለሁ።

122 ጌታ አባት ሆይ፤ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤ ይሄን ገስጽሁ። የእግዚአብሄር ሃይል፤ የእግዚአብሄር ፈውስ... በሚቀጥሉት አምስት ደቂቃዎች በእሱ ዘንድ ዓይነተኛ ለውጥ ይሁን... ? ... ነገር ሁሉ... ? ... ለክብርህ ይሁን።

123 የሰማይ አባት ሆይ፤ ቃልህን ሰጥተሀል። የማውቀውም ይህ ነው፤ ቃልህን መስጠትህ። “እንዲህ ካልከው” እንደተባለው፤ ሆኗል፤ ይህን ጉባኤ እያሰረ ላለው ህመም እና ዲያብሎስ ሁሉ እናገራለሁ፤ ህዝቡን ያሰረ፤ እያንዳንዱ

ያለማመን መንፈስ፤ እላለሁ፦ “በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤ ህዝቡን ልቀቅ!” እንደተፃፈ እናውቃለን፤ አሁን ግን፤ ስለ እግዚአብሄር ክብር፤ እና ሞገስ፤ ይሁን ተባለ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን።

124 አሁን፤ አማኝ የሆናችሁ፤ እና እምነት ያላችሁ፤ ምንም ቢሆን ምንም፤ እንደተጣለ ዘር፤ መሆን የለባችሁም። ያ በእናንተ ውስጥ ያለው ደቃቅ ነገር፤ ያ ድምጽ። የዚህ ልጅ ወላጆች ፣ የልጁ ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፤ የእግዚአብሄር ዘር በልባችሁ ዘንድ እንዳረፈች፤ ልጁም እንደሚፈወስ ታምናላችሁ? ሌሎቻችሁ፤ አንዱ ለሌላው ይጸልይ። የእግዚአብሔር ዘር በልባችሁ ውስጥ እንደገባ ታምናላችሁ፤ “ሕመሜ አበቃለት”? የእምነት ጸሎት ስለተጸለየላችሁ፤ ታቤላውን አውርዱ። ሰይጣን ተመልሶ ለመምጥት ቢሞክር፤ መለሰ ብላችሁ፤ “በሰፓኒሿ ቤተክርሰቲያን ውስጥ ሆኜ፤ እሁድ ጠዋት፤ የእምነት ጸሎት ተደርጎልኛል። እግዚአብሔርም ቃል ገብቷል!” የእምነት ጸሎት ሕመምተኛውን ትፈውሳለች እግዚአብሄርም ያነሳቸዋል። ይህ እንዲሆን ግድ ነው። ታምናላችሁ? “አሜን።” በሉ፤ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አሁን ጉባኤውን ለወንድም ሮዝ ልሰጥ፤ ወንድም ጄወል ሮዝ፡ እዚህ ያለ ይመስለኛል።

**የእግዚአብሔር ድምጽ በነዚህ የመጨረሻ ቀናት** AMH63-0120M

(The Voice Of God In This Last Days)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ጠዋት፤ ጥር 20, 1963, በፊኒክስ፤ አሪዞና በሚገኝ ሐዋርያዊት ቤተክርሰትያን፤ ዩ.ኤስ.ኤ.: ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2021 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org